# የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን
# የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር
# መመሪያ 02/2012



The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Coffee & Tea Development & Marketing Authority

መስከረም 2012
አዲስ አበባ

**የቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር አፈፃፀም መመሪያ**

**ቁጥር - 002/2012**

የቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1051/2009 እና በቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 433/2011 ላይ የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን ለማስፈጸም በማስፈለጉ፤

በቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1051/2009 አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 2 ለኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን በተሰጠው ስልጣን መሠረት የቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር መመሪያ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ ድንጋጌዎች**

**1.1አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር አፈጻፀም መመሪያ ቁጥር - 002/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፣

**1.2ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"አዋጅ"** ማለት የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1051/2009 ማለት ነው፡፡
2) **"ደንብ "** ማለት የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 433/2011 ማለት ነው፡፡
3) **"የቴክኒክ መስፈርቶች"** ማለት የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች፣ የቡና ዕሴት ጨማሪ ኢንዱስትሪዎች፣ ጥራትና ጣዕም ምርመራ ላብራቶሪዎች፣ የማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች የውስጥ አደረጃጀትና አሰራር ጥራትና ብቃት አመላካች የሆኑ መስፈርቶች ናቸው፡፡
4) **"የቡና መያዣ ጆንያ"** ማለት እሸት ወይም ጀንፈል ወይም የአቅርቦት ወይም የኤክስፖርት ቡና ከቦታ ቦታ ለማዘዋወር ወይም ለማከማቸት ጥቅም ላይ የሚውል ከቃጫ ወይም ለቡና ተስማሚነታቸው አግባብ ባለው አካል በተረጋገጡ ግብዓቶች የተሰራ ከረጢት ነው፡፡
5) **"የኮንትራት ቡና ልማት /contract coffee farming/ ወይም የአምራችና ኢንዱስትሪ ትስስር"** ማለት በቡና አምራችና በወጪ ቡና ቆይ ኢንዱስትሪዎች መካከል በውልና በተፈቀደ አሰራር የሚፈፀም የቡና ግዢና ሽያጭ ነው፡፡
6) **"ውል"** ማለት፡- በቡና ልማትና ግብይት ሂደት ውስጥ በሁለቱ እና ከዚያ በላይ በሆኑ ተዋዋይ ወገኖች የሚፈጸም ሕጋዊ የስምምነት ሰነድ ነው፡፡
7) **"የውል ስምምነት ይዘት"** ማለት፡- ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች በውል ስምምነት ሰነዳቸው በአስገዳጅነት ሊያሟላቸው የሚገቡ የውል ቃሎች ናቸው፡፡
8) **"ሕገወጥ ቡና ማለት"**፡- በአዋጁና በደንቡ ከተደነገጉት ህጋዊ የቡና ግብይት፣ ዝግጅት ፣ ክምችትና ማጓጓዝ ስርዐት ውጪ የሆነ ቡና ነው፡፡



ዶ/ር ደበላ ቦቴ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

9) "ጥቆማ" ማለት፡- ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል ወይም ለሕግ አስከባሪ አካል ስለሕገወጥ ቡና የሚቀርብ መረጃ ወይም ማስረጃ ነው፡፡

10) "ጠቋሚ" ማለት፡- በማናቸውም ሁኔታ ስለህገወጥ ቡና እንቅስቃሴ ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል መረጃ የሚያቀርብ ሲሆን ማንኛውንም የሕግ አስከባሪ ተቋም አባል ወይም የባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ሠራተኛን አይጨምርም፡፡

11) "ያዥ" ማለት፡- ሕገወጥ ቡናውን ይዞ ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል ገቢ ያደረገ ሰው ወይም አካል ሲሆን ማንኛውንም የባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ሠራተኛን አይጨምርም፡፡

12) "ቋሚ ንብረት" " ማለት ግዙፋዊ የሆነ እና አግባብ ባለው የመንግሥት አካል የተመዘገበ የማይንቀሳቀስ ንብረት ነው፡፡

13) "ለሃገር ውስጥ ፍጆታ የማይመጥን ቡና" ማለት ተረፈ ምርት ቡና ሆኖ የቡናው ፍሬ መልክ ወደ ጥቁር የተቀየረና በጤና ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚገመት ቡና ነው፡፡

14) **አገልግሎቱን ያጠናቀቀ የቡና ቅጠል፡-**

15) በአዋጁ እና በደንቡ ላይ የተመለከቱት ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያ አፈጻፀም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

### 1.3 የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዋጁ አንቀጽ 3 በተጠቀሱ አካላት ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የብቃት ማረጋገጫ የቴክኒክ መስፈርቶች

### 2.1 የታጠበ የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማካማቻ ኢንዱስትሪ የቴክንክ መስፈርት

ማንኛውም የታጠበ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ወደ ማዘጋጀቱና ማከማቸቱ ሥራ ከመግባቱ በፊት የሚከተሉትን የቴክኒክ መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት አለበት፡-

1) አጠቃላይ የቦታ ስፋት ከ2 ሄ/ር ያላነሰ ሆኖ ተዳፋታማነቱ ከ10-15% የሆነ መሬት ላይ ያረፈ መሆን አለበት፣

2) አነስተኛ ይዞታ ያለው አርሶአደር ከሆነ ያመረተውን ምርት ለመፈልፈል የሚያገለግል አነስተኛ ማሽን፣ ምርቱን ለማጠብ፣ለማድረቅና ለማከማችት የሚመጥን መጋዘን ለመገንባት የሚያስችል በቂ ቦታ ያለው፤

3) በኢንዱስትሪው የቡና ግብይት የሚካሄድበት ከሆነ የተለየ ጥላ ያለው በቂ ቦታ ያዘጋጀ፤

4) በአከባቢዉ በየዓመቱ 100 ቶን የእሸት ቡና ምርት ለዝግጅቱ ሊቀርብ የሚችል ከሆነ፣

5) ከወንዝ ያለው ርቀት የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ያወጣውን መስፈርት መሰረት ያደረገና ከኢንዱስትሪው የሚወጣውን ፍሳሽ ማጠራቀሚያነትና ለማስወገጃነት የሚውል ጉድጓድ/ላጉን/ የሚጠቀም፣

6) ቀይ እሸት ቡና ጥራት መፈተሻ ጥላ ያለው እና ጠረጴዛ (SortingTable) የሚጠቀም፣

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Coffee & Tea Development & Marketing Authority



ጂዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

7) በሲምንቶ የተሰራ ቢያንስ 0.6 ሜትር ኪዮብ የመያዝ አቅምና ጥልቀቱ ከአንድ ሜትር ያልበለጠ የቡኬት ገንዳዎች የተሠራለት፣

8) የማጠቢያ ቦይ (Washing canal) አሰራር 2 ሣንቲ ሜትር ተዳፋትነት ጠብቆ የተሰራ፣ ስፋቱ 90 ሣንቲ ሜትር ፣ ጥልቀቱ 45 ሣንቲ ሜትር እንዲሁም ርዝመቱ 17 ሜትር የተዘጋጀለት፤

9) ለመጀመሪያ ደረጃ ድርቀት (Skin Drying) ማከናወኛ ስፋቱ 2 ሜትር በ1ሜ እና ጥልቀቱ 5 ሣ/ሜ የሆነ ቢያንስ 400 ባለ እጀታ ተንቀሳቃሽ ወንፊቶች የሚጠቀም፣ እንዲሁም 60 ባለ 12.5 ሜትር በ2 ሜትር ስፋት ያለውና ከመሬት ከ90 ሣንቲ ሜትር እስከ 1 ሜትር ከፍ ያለ የመጨረሻ ድርቀት ማከናወኛ አልጋ (Main drying bed) ያለው፤

10) በተዘጋጀው አልጋ ላይ ለቡና ማስጫነት የሚያገለግል ከቃጫ የተሠራ ከማንኛውም የኬሚካል ቅሪት ነፃ የሆነ ብትን/ዝርግ ጆንያ እና ባለ 30 ማይክሮንስ ውፍረት ያለው ከኬሚካል ቅሪት ንፁሕ የሆነ ብትን ፕላስቲክ የሚጠቀም

11) በአከባቢው ቋሚ ፍሰት ያለዉ ወንዝ ወይም ለቡና እጥበት ተስማሚ የሆነ በቂ ዉሃ ሊያመነጭ የሚችል ጥልቅ የዉሃ ጉድጓድ ወይም ውሃን የማይጠቀም ወይም በጣም አነስተኛ ውሃ የሚጠቀም ቴክኖሎጂ ከሆነ አንጻራዊ የሆነ በቂ ውሃ ከማንኛውም የውሃ መገኛ ምንጭ ያለው፣

12) ውሃ ቆጣቢ፣ የአከባቢ ብክለት የማያስከትል እና በሰዓት ቢያንስ አንድ ቶን እሸት ቡና የመፈልፈል አቅም ያለዉ ማሽን የሚጠቀም፣

13) በኢንዱስትሪው ጥቅም ላይ የዋለዉን ዉሃ መልሶ ለመጠቀም (Recycling) የሚያስችል ተክኖሎጂ የሚጠቀም ወይም ለቡና እጥበት ጥቅም ላይ የዋለ ዉሃ ማጣሪያ ተፈጥሯዊ አሠራር የሚጠቀም ወይም ቬትቫር ሣር የተተከለ

14) ከአርሶ አደር በስተቀር ኢንዱስትሪውን የሚያንቀሳቅስ ራሱን የቻለ ከማንኛውም የኃይል ምንጭ የኤሊክትሪክ ኃይል ያለውና ለስርጭቱም መሥመር የተዘረጋለት፣

15) የመጋዘኑ ስፋት አስራ አምስት ሜትር በሃያ ሜትር ስፋትና ስድስት ሜትር ከፍታ ያለው ግድግዳዉ በብሎኬት ወይም በሌላ ተስማሚ ቁሳቁስ፣ ወለሉ በስሚንቶ የተሰራ እና ለአየር ማስገቢያ የሽቦ ወንፊት የተገጠመለት ወይም ዘመናዊ የአየር ማስገቢያና ማስወጫ ማሽን የሚጠቀም መጋዘን፣

16) ቡና ለመጫንና ለማራገፍ በቂ የተሽከርካሪ ማቆሚያና ማስገቢያ መንገድ ያለዉ፣

17) አግባብ ባለው አካል ብቃቱ የተመረመረ ሚዛንና የእርጥበት መለኪያ መሳሪያዎች ያሉት፣

18) በመጋዘን ውስጥ ከእንጨት ወይም ከፕላስቲክ የተሰራ (wooden or plastic pallet) የቡና መደርደሪያ ያለዉ፣

19) ቡናን በማዘጋጀት ሂደት በተፈጥሮ አከባቢ፣ በአከባቢው በሚገኝ ማህበረሰብ ወይም በግለሰብ ጤንነት ላይ ጉዳት በማያስከትል አኳኋን ቆሻሻን ለማስወገድ የሚያስችል አሠራር የሚጠቀም፣

20) የኢንዱስትሪውን ማሽኖች ለማንቀሳቀስ የሚችል ክህሎት ያለው ባለሙያ ያሠማራና ለዚሁ ከቴክኒክና ሙያ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ወይም አግባብ ያለው የስራ ልምድ የሚያቀርብ፣



አዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

21) በማዘጋጃዉ ኢንዱስትሪው ለሚሠሩ ሰራተኞች የሚያገለግል ሽታ የማይቀበልና በውሃ በቀላሉ የማይርስ ገዋን፣ የእጅ ጓንት፣ የራስ ፀጉር መሸፈኛ እና ተስማሚ ቦቲ ጫማ ያዘጋጀ፣

22) ለቡና ማዘጋጃዉ ሠራተኞች የተሟላ ጾታን ያማከለ መጸዳጃ ቤት፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃ እና መታጠቢያ ቤት ያለዉ፣

23) የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ ያለው፣

## 2.2 ያልታጠበ የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማካማቻ ኢንዱስትሪ የቴክንክ መስፈርት

ማንኛውም ያልታጠበ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ወደ ማዘጋጀቱና ማከማቸቱ ሥራ ከመግባቱ በፊት የሚከተሉትን የቴክኒክ መስፈረቶች አሟልቶ መገኘት አለበት፡-

1) ያልታጠበ ቡና የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ለማቋቋም የሚያስፈልገው የቦታ ስፋት ከ1 ሄክታር ማነስ የለበትም፣

2) በቡና ጥራት ላይ ጉዳት የማያስከትል ኃይል ቆጣቢ እና ቢያንስ በሰዓት 2 ቶን ቡና መቀሸር የሚችል ማሽን ያለው፣

3) በኢንዱስትሪው ግብይት የሚካሄድበት ከሆነ የተለየ ጥላ ያለው በቂ ቦታ ያዘጋጀ፤

4) ጀንፈልና ቅሽር ቡናን ለያይቶ ማከማቸት የሚያስችል ሲፋቱ ቢያንስ 600 ኬሻ የሚይዝ ግድግዳዉ ከብሎኬት እና ወለሉ ከስሚንቶ የተሠራ የመጋዘኑ የግድግዳ ጫፍ ለአየር ማስገቢያ ወንፊት ሽቦ የተገጠመለት ወይም ዘመናዊ የአየር ማስገቢያና ማስወጫ ማሽን የሚጠቀም፣

5) ስፋቱ 500 ካሬ ሜትር የሆነ ከስሚንቶ የተሠራ በቂ የጀንፈል ቡና ማድረቂያ አውድማ ወይም ቢያንስ 20 ሜትር ርዝመት ያለዉ ከመሬት አንድ ሜትር ከፍ ብሎ 2 ሜትር በ1 ሜትር ስፋት ያለዉ በአከባቢ ቁሳቁስ ወይም ከሽቦ የተሰራ የማድረቂያ 25 አልጋ ያለው፤

6) የጀንፈል ቡና ቋት ከብረት የተሠራና ቡና የመያዝ አቅሙ ከማጣሪያ ማሽኑ አቅም ጋር ተመጣጣኝ የሆነ፣

7) ቅድመ ማጣሪያ (pre-cleaner) ባዕድ ነገሮችን ማለትም ድንጋይ፣ እንጨት፣ ጥራጥሬ፣ ቅጠላ ቅጠል፣ ቀንበጥ እና ብረት ነክ ለይቶ ለማስወገድ የሚያስችል የማበጠሪያ መሣሪያ የሚጠቀም፣

8) ማሽኑ የተጣራውን ጀንፈል ቡና ወደ መቀሸሪያ (Huller) የሚያስተላልፍ አካል (Conveying belt & socket) ያለው፣

9) የቡናውን ፍሬ አካል በሙቀትም ሆነ በመስበር ያማይጎዳ መቀሸሪያ (Huller) የሚጠቀም፤

10) የተቀሸረውን ቡና ፍሬ ከገለባው መለያ (Pneumatic aspirator) የሚጠቀም፣

11) የደረጃ መለያ ወንፊት (Circular careen) የሚጠቀም፤

12) የተቀሸሩ የተሰባበሩና ሌሎች ቀላል ፍሬዎች በንፋስ ኃይል ለመለየት የሚረዳና ቡናዎቹን በክብደታቸው መጠን ከሦስት እስከ ሰባት የክብደት ደረጃ የሚለይ ካታዶር የሚጠቀም፣

13) ኢንዱስትሪውን የሚያንቀሳቅስ ራሱን የቻለ ከማንኛውም የኃይል ምንጭ የኤሌክትሪክ ኃይል ያለውና ለስርጭቱም መሥመር የተዘረጋለት፣



እዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

14) የኢንዱስትሪውን ማሽኖች ለማንቀሳቀስ የሚችል ክህሎት ያለው ባለሙያ ያሠማራና ለዚሁ ከቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ወይም አግባብ ያለው የስራ ልምድ የሚያቀርብ፣

15) ቡና የጫነ ተሽከርካሪ ወደ ግቢው ማስገቢያና ማስወጫ መንገድና በቂ ማቆሚያ ቦታ ያለው፣

16) በማሽኑ የተቀሸረ ቡናን ለማበጠርና ለቅሞ ለማጣራት በቂ የቡና መልቀሚያ ቦታ ያለው፣

17) ለቡና ማዘጋጃዉ ሠራተኞች የተሟላ ጾታን ያማከለ መጸዳጃ ቤትና መታጠቢያ ቤት ያለዉ፣

18) በመጋዘኑ ውስጥ ከእንጨት ወይም ከፕላስትክ የተሠራ (wooden or plastic pallet) የቡና መደርደሪያ ያለዉ፤

19) የምርት ዝግጅት እንደተጠናቀቀ ለምርት መያዣ የሚሆን ከቃጫ የተሠራና ከማናቸዉም ባዕድ ሽታ እና ኬሚካል ቅሪት የጸዳ ጆኒያ የሚጠቀም፣

20) የመቀሸሪያ ማሽኑን ለማጽጃ የሚሆን የንፋስ መንፊያ (Air blower) ማሽን ያለው፤

21) በማዘጋጃ ኢንዱስትሪው ለሚሠሩ ሰራተኞች የሚሆን ሽታ የማይቀበልና በውሃ በቀላሉ የማይርስ ገዋን፣ የእጅ ጓንት፣ የራስ ፀጉር መሸፈኛ እና ተስማሚ ጫማ ያለው፣

22) አግባብ ካለው አካል ብቃቱ የተመረመረ ሚዛንና የእርጥበት መለኪያ መሳሪያዎች ያሉት፣

23) ከማበጠሪያ ኢንዱስትሪዉ የሚወጣዉ ብጣሪና ገለባ አከባቢዉን እንዳይበክል የማስወገጃ ሥርዓት ያለዉ፣

24) የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ ያለው፣

## 2.3 የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ የቴክንክ መስፈርት

ማንኛውም የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ወደ ቡና ማዘጋጀትና ማከማቸት ሥራ ከመሠማራቱ በፊት የሚከተሉትን መሥፈርቶች አሟልቶ መገኘት አለበት፡-

1) የአቅርቦት ቡና ማከማቻ ስፋቱ ቢያንስ 20 ሜትር በ 15 ሜትር እና የተዘጋጀ ቡና መከማቻ ስፋቱ 20ሜትር በ 15ሜትር የሆነ ግድግዳዉ ክብሎኬት ወለሉ ከስሚንቶ የተሠራ የመጋዘኑ የግድግዳ ጫፍ ለአየር ማስገቢያ ወንፊት ሽቦ የተገጠመለት ወይም ዘመናዊ የአየር መሳቢያና ማስወጫ መሣሪያ የተገጠመለት መጋዘን ያለዉ ፤

2) የማበጠሪያ ማሽኑ ቢያንስ በቀን 36 ቶን እና ከዚያ በላይ ቡና ለወጪ ገበያ ማዘጋጀት አቅም ያለው ሲሆን፣ ከመጋዘኑ ጋር ተያይዞ የተገነባ ቡና መጫኛና ማራገፊያ በረንዳ ያለው፣

3) ቡና የጫነ ተሽከርካሪ ወደ ግቢው መስገቢያ መንገድ፣ በግቢው መኪና መዘዋወርያና በቂ ማቆሚያ ቦታ ያለው፣

4) የማበጠሪያ መሣሪያ ቋት፣ ቅድመ ማበጠሪያ (Pre cleaner) የንፋስ መለኪያ (pneumatic aspirate) ፣ በክብደት ደረጃ መለያ (Densmetric Separator) and grader) እና በመጠን መለያ ወንፊቶች (Screen grading) ያለው፣

5) የኢንዱስትሪውን ማሽኖች ለማንቀሳቀስ ከሥራው ጋር አግባብነት ያላቸው ባለሙያዎች ያሠማራ፣

6) የመጋዘን የውስጥና የውጭ ሙቀትና ምዝን የአየር ዕርጥበት /Temperature and Humidity/ ከ20- 22 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሆኖ እንዲቆይ የሚቆጣጠር አውቶማቲክ መሳሪያ /air Conditioner/



ዶ/ር አዱኛ ደበላ ቡቴ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

7) የጠቆሩ፣ የገረጡና በሻጋታ የበለዙ፣የተሰባበሩ የቡና ፍሬዎችን እና ሌሎች ባዕድ አካላትን ለይቶ ለማውጣት የሚያስችል ኤሌክትሮኒክ መለያ መሳሪያ (Uv light) ወይም የቀለም መለያ /Color sorter) ያለው፣

8) ብትን ቡናን በኮንቴነር ለማስጫን የሚያስችል የብሎዌር ማሽን ያለው፣

9) ለምርት መያዣ የሚሆን ከቃጫ የተሠራና ከማናቸውም ባዕድ ሽታ የነጻ ጆንያ የሚጠቀም፣

10) ከሚመለከተዉ የመንግስት ተቋም ብቃቱ ተመርምሮ የተመሠከረለት የምድር ሚዛንና የእርጥበት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች ያሉት፣

11) የቡና ጥራትና ጣዕም መለያ ላቦራቶሪ እና የቡና ጣዕም ምርመራ ባለሙያ ያለው፣

12) ማንኛውም ለውጭ ገበያ የተዘጋጀ ቡና መያዣ ኬሻ ላይ አስፈላጊ መረጃዎች (Labeling) የሚያትምና የሚያሽግ መሳሪያ ያለው፣

13) በማዘጋጃ ኢንዱስትሪው ለሚሠሩ ሰራተኞች ለሥራ አገልግሎት ብቻ የሚውል በቀላሉ በውሃ የማይርስና ሽታ የማይቀበል ገዋን፣ የእጅ ጓንት እና ለዚህ አገልግሎት የሚውል ጫማ ያለው፣

14) ለቡና ማዘጋጃዉ ሠራተኞች ፆታን ያማከለ የተሟላ የንጽህና መጠበቂያ ቦታ፣ መጸዳጃ ቤትና መታጠቢያ ያለዉ፣

15) የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ ያለው፣

## 2.4 ለውጪ ገበያ የተሸጠ ቡና ማከማቻ ጥብቅ መጋዘን (Bonded Warehouse) የቴክኒክ መስፈርት

በማንኛውም አካል የተገነባ የተሸጠ የወጪ ቡና ማከማቻ ጥብቅ መጋዘን ወደ ቡና ማከማቸት ሥራ ከመሠማራቱ በፊት የሚከተሉትን መሥፈርቶች አሟልቶ መገኘት አለበት፡-

1) ቡናን ለማከማቸት እና ለመጫን የሚያስችል ስፋቱ 20ሜትር በ50 ሜትር ያላነሰ፣ ወለሉ ከሲምንቶና ግድግዳዉ ከብሎኬት የተሰራ፣ ሁለት ሰፋፊ በሮች ያሉት እና ሙቀትና ቅዝቃዜን የሚቆጣጠር የአየር ማስገቢያ እና ማስወጫ መሣሪያ ያለዉ፣

2) አግባብ ባለው አካል የተመሰከረለት ሚዛንና የእርጥበት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች ያሉት፣

3) ለቡና ምርት መደርደሪያ የሚያስፈልግ ከእንጨት ወይም ተስማሚ ከሆነ ፕላስቲክ ወይም ከጣውላ የተሠራ ከማከማቻው ስፋት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ መደርደሪያ (wooden or plastic pallet) ወይም ሌላ ዘመኑ ያፈራው ቴክኖሎጂ ያለዉ፤

4) ቡናን ለመጫንና ለማራገፍ ቢያንስ ሁለት መኪና ከነተሳቢው ማቆሚያና ማስገቢያ መንገድ ያለዉ፣

5) የቡና ማከማቻ መጋዘኑ ከወንዝና እርጥበት ሊያመጡ ከሚችሉ አካባቢዎች በተለይም ሽታ ሊፈጥሩ ከሚችሉ ቦታዎች የራቀ፣

6) መጋዘኑ አስተማማኝ የሆነ የሰው እና የቴክኖሎጂ ጥበቃ ስርዓት ያለው፤

7) የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ ያለው፡፡



እዱኛ ደበላ ቡቴ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

## 2.5 የቢሮና የሰው ኃይል አደረጃጀት መስፈርቶች

1/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው የቢሮ እና የሰው ኃይል አደረጃጀት የቴክኒክ መስፈርት፡-

ሀ/ ቢሮው ለድርጅቱ ሠራተኞች የሚሆን ወንበርና ጠረጴዛ፣ ፋይል ማደረጃ ሼልፍ፣ ስልክ እና ኮምፒውተር ከነፕሪንተር ያሟላ፣

ለ/ የቡና ምርት እንቅስቃሴ መረጃ ለማደራጀት፣ለመተንተንና ለማስራጨት የሚያስችል የአሰራር ሥርአት የዘረጋ

2/ በድርጅቱ ስም የሚከተሉትን ሠራተኞችን በቋሚነት የቀጠረ፣

ሀ/ ሥራ አስኪያጅ ቢያንስ በድፕሎማ የተመረቀ/ች

ለ/ የሒሳብ ሰራተኛ በአካዉንቲንግ ቢያንስ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች፣

ሐ/ የቡና ጥራት ባለሙያ ቢያንስ ከሥራ መስኩ ጋር በተዛማጅ የትምህርት ዝግጅት ዲፕሎማ ያለው እና በቡና ቀማሽነት ሙያ ባለፉት ሁለት ዓመታት ያገለገለ፣

መ/ የቡና ክምችት አዘገጃጀትና ጥራት አያያዝ ባለሙያ ቢያንስ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች፣

ሠ/ የቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ልዩ ሙያ ያለው/ ያላት ሆኖ የሙያ ብቃቱ በሚመለከተው ሕጋዊ አካል የተረጋገጠ እንዲሁም በቀማሽነት ያገለገለ ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣

ረ/ በቡና መቁላት፣ መፍጨትና ማሸግ ልዩ ሙያ ያለው/ያላት፣

## 2.6 የውጪ ቡና ቆዪ ኢንዱስትሪ የቴክንክ መስፈርት

1) ወለሉ ከሴራሚክስ፣ ግድጋዳው ከብሎኬት ተሠርቶ በውሃ ሊታጠብ በሚችል ቀለም የተቀባ፣ አየር ማስገቢያና ማስወጫ አሠራር የሚጠቀም ወይም ለዚሁ ተግባር የተሰራ መስኮት ያለው ቢያንስ ስፋቱ 100 ካሬ ሜትር ማከማቻ መጋዘን ያለው፣
2) በኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን ብቃቱ የተመሰከረለት የኤሌክትሪክ የቡና ሙቂያ ማሽን ቢያንስ በሰዓት 100 ኪሎ ግራም መቁላት የሚችል፣ በሰዓት 50 ኪ/ግ የተቆላ ቡና መፍጨት የሚችል የኤሌክትሪክ ቡና መፍጫ ያለው፣
3) ብቃቱ የተረጋገጠ የቡና ጥራትና ጣዕም ምርመራ ላቦራቶሪ ያለው፣
4) በሚመለከተው አካል ብቃቱ የተመሠከረለት ተቆልቶ ወይም ተፈጭቶ ለተዘጋጀ ቡና ማሸጊያ የሚሆን ውስጡ በአሉሚኒየም የተለበደ (Aluminum coated)፣ የአየር ማስተንፈሻ ያለው፣ በውጭ ሽፋኑ ላይ በውስጡ የያዘውን ቡና ዓይነት፣ የጥራት ደረጃ፣ የተመረተበት እና የመጠቀሚያ ጊዜ፣ የኢትዮጵያ ምርት ስለመሆኑ በትክክል የሚገልፅ ጽሁፍ ለማተም የሚያስችል መሣሪያ ያለው
5) የተቆላና የተፈጨ ቡና አየር የማያስገባ ማሸጊያ መሣሪያ ያለው፣
6) የመቂያና የመፍጫ ማሽኖች አንቀሳቃሽ ባለሙያ ያለው፣



አዱኛ ደበላ ቡቴ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

7) ለሠራተኞቹ የራስ ፀጉር፣ የአፍንጫና የአፍ መሸፈኛ ልብስ የተዘጋጀለት፣ የእጅ ጓንት፣ በተለየ ሁኔታ የተዘጋጀ ቱታ ወይም ልብስ የተዘጋጀለትና ለዚሁ ተግባር ተስማሚ ጫማ፣ ለሠራተኞቹ የልብስ መቀየሪያና መታጠቢያ ክፍሎች ሲኖር፣

8) ከኢንዱስትሪው የሚወጣ ሽታ፣ ብጣሪና ገለባ አካባቢውን እንዳይበክልየአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የሚያወጣውን ደረጃ የጠበቀ ማስወገጃ ስርዓት ያለው፣

9) ቡናን ለመጫንና ለማራገፍ በቂ የተሽከርካሪ ማቆሚያና የሚያስገባ መንገድ ሊኖረው ይገባል፣

10) የእሳት አደጋ መከላከያ ያለው፡፡

## 2.7 የሃገር ውስጥ ቡና ቆዪ ኢንዱስትሪ የቴክንክ መስፈርት

1) ወለሉ ከሴራሚክስ፣ ግድጋዳው ከብሎኬት ተሠርቶ በውሃ ሊታጠብ በሚችል ቀለም የተቀባ፣ አየር ማስገቢያና ማስወጫ አሠራር የሚጠቀም ወይም ለዚሁ ተግባር የተሰራ መስኮት ያለው ቢያንስ ስፋቱ 50 ካሬ ሜትር ማከማቻ መጋዘን ያለው፣

2) በኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን ብቃቱ የተመሰከረለት የኤሌክትሪክ የቡና ሙቂያ ማሽን ቢያንስ በሰዓት 50 ኪሎ ግራም መቁላት የሚችል፣ በሰዓት 25 ኪ/ግ የተቆላ ቡና መፍጨት የሚችል የኤሌክትሪክ ቡና መፍጫ ያለው፣

3) ብቃቱ የተረጋገጠ የቡና ጥራትና ጣዕም ምርመራ ላቦራቶሪ ያለው፣

4) በሚመለከተው አካል ብቃቱ የተመሠከረለት ተቆልቶ ወይም ተፈጭቶ ለተዘጋጀ ቡና ማሸጊያ የሚሆን ውስጡ በአሉሚኒየም የተለበደ (Aluminum coated)፣ የአየር ማስተንፈሻ ያለው፣ በውጭ ሽፋኑ ላይ በውስጡ የያዘውን ቡና ዓይነት፣ የጥራት ደረጃ፣ የተመረተበት እና የመጠቀሚያ ጊዜ፣ የኢትዮጵያ ምርት ስለመሆኑ በትክክል የሚገልፅ ጹህፍ ለማተም የሚያስችል መሣሪያ ያለው

5) የተቆላና የተፈጨ ቡና አየር የማያስገባ ማሸጊያ መሣሪያ ያለው፣

6) የመቁያና የመፍጫ ማሽኖች አንቀሳቃሽ ባለሙያ ያለው፣

7) ለሠራተኞቹ የራስ ፀጉር፣ የአፍንጫና የአፍ መሸፈኛ ልብስ የተዘጋጀለት፣ የእጅ ጓንት፣ በተለየ ሁኔታ የተዘጋጀ ቱታ ወይም ልብስ የተዘጋጀለትና ለዚሁ ተግባር ተስማሚ ጫማ፣ ለሠራተኞቹ የልብስ መቀየሪያና መታጠቢያ ክፍሎች ሲኖር፣

8) ከኢንዱስትሪው የሚወጣ ሽታ፣ ብጣሪና ገለባ አካባቢውን እንዳይበክል የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የሚያወጣውን ደረጃ የጠበቀ የማስወገጃ ስርዓት ያለው፣

9) ቡናን ለመጫንና ለማራገፍ በቂ የተሽከርካሪ ማቆሚያና የሚያስገባ መንገድ ሊኖረው ይገባል፣

10) የእሳት አደጋ መከላከያ ያለው፡፡

## 2.8 የቡና ጣዕምና ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ የቴክኒክ መስፈርት

ማንኛውም የቡና ጣዕምና ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ ወደ ቡና ጣዕምና ጥራት ምርመራ ሥራ ከመሠማራቱ በፊት የሚከተሉትን መሥፈርቶች አሟልቶ መገኘት አለበት፡-

1) አንድ የቡና ናሙና መቀበያና ማዳራጃ ፣አንድ የቡና መቁያ፣ መፍጫ፣ ውሃ ማፍያ እና ንጽህና መጠበቂያ እና አንድ የጥሬ ቡና መለያ፣ የተቆላ ቡና መለያ እና የተፈላ ቡና ጣዕም መለያ ስኒ ማስቀመጫ ጠረጴዛዎች እና ወንበሮች መያዝ የሚችል ሦስት ክፍሎች ያሟላ፣

2) የጥሬ ቡና ጥራት መለያ፣ የተቆላ ቡና ጥራት መለያ እና የተፈጨ ቡና ጥራት መለያ ትሪዎች፣ የቡና ጣዕም መለያ ኩባያዎች፣ ቡና መቅመሻ ማንኪያዎች፣ መትፊያ ኩባያዎች፣ ቆሻሻ መጣያ ባልዲዎች ያሉት፣

3) በኤሌክትሪክ የሚሠራ የቡና መቁያ ማሽን እና መፍጫ ማሽን ያለው፣

4) የናሙና አውጪ ሰራተኛ፣ ናሙና ተቀባይና አደራጅ ሰራተኛ፣ ቡና ቆይ፣ ፈጪና አፍልቶ ለቀማሾች አቅራቢ ሰራተኛ፣ ቡና ቀማሽ ባለሙያዎች እና የጽዳት ሠራተኛ አደራጅቶ የያዘ፣

5) ቅሬታዎችን ለማስታረቅ ሲባል ለአንድ ወር ያህል ቡናውን በቀሪ ናሙና በዓይነቱ ተለይቶ ለማስቀመጥ የሚያስችል መደርደሪያ ወይም ሣጥን ያለው፣

6) አነስተኛ ዲጂታል ሚዛን፣ የዕርጥበት መለኪያ እና ናሙና ማሸጊያ መሣሪያዎች ያሉት፣

7) የቡና ጉድለቶች መለያ ባትሪ (UV Light) ያለው፣

8) ዓለም አቀፍ የጥራት ጉድለት ደረጃ (Defect standard) በወጣላቸው የጥሬ ቡና ጉድለት ዓይነቶች በመቁጠርና የጥራት ነጥብ በመስጠት የሚከናወን የአሠራር ቴክኒክ ያለው፣

## 2.9 ቡና የሚጭን ተሽከርካሪ የተክኒክ መስፈርት

ማንኛውንም ቡና የሚጭን ተሽከርካሪ ወደ ቡና ጭነት ሥራ ከመሠማራቱ በፊት የሚከተሉትን መሥፈርቶች አሟልቶ መገኘት አለበት፡-

1) ተሽከርካሪዉ ለጭነት አገልግሎት እንዲውል ፈቃድ ያለውና መለያ ሰሌዳ ቁጥር ሲኖረው፣

2) ቡና የሚጭን ተሽከርካሪ ቢያንስ 35 ኩንታል ወይም በኮንቴነር ከሆነ 20 ፊት ኮንቴነር የመሸከም አቅም ያለው፣

3) መኪናው ቡና በሚያስጭን አኳኋን ታጥቦና ንፅህናው ጠብቆ ለቡናው ጥራት የማይጎዳ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

4) የጭነት ተሽከርካሪ ቡናውን ከፀሐይ፣ ከዝናብ፣ ከአቧራና ከልዩ ልዩ ባዕድ ነክኪዎች መጠበቅ የሚችል ካኪ ሸራ፣ መወጠሪያና ማሠሪያ ገመድ እንዲሁም በክረምት ወቅት ከሸራ በላይ ተጨማሪ የላስቲክ ሽፋን ያለው፣

5) የታደሰ ተሽከርካሪው የሶስተኛ ወገን የመድህን ዋስትና ሰርቲፊኬት ያለው፣

6) የጭነት መኪናው ከትራንስፖርት ባለስልጣን የታደሰ የማሽከርከር መንጃ ፈቃድ የያዘ አሽከርካሪ ወይም ሹፌር የተቀጠረለት ሲሆን፣

7) የተሽከርካሪው ህጋዊነት ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም የተረጋገጠለት ሰነድ (ሊብሬ) ያለው፣

8) ዓመታዊ የጭነትና የመሽከርከር ብቃት ምርመራ ስለማጠናቀቁ ሰነድ ያለው፣

## 2.10 የቡና ገለባ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ የቴክኒክ መስፈርት

ማንኛውም የቡና ገለባ አቀነባባሪ ኢንዱስትሪ ወደ ቡና ገለባ ማቀነባበር ሥራ ከመሠማራቱ በፊት የሚከተሉትን መሥፈርቶች አሟልቶ መገኘት አለበት፡-

1) የቡና ገለባውን ለተለያዩ አገልግሎቶች ለማቀነባበር ሚያስፈልገው የማቀነባባሪያና የምርት ማደራጃ ቦታ ሊኖረው ይገባል፤
2) የቡና ገለባ ማከማቸት የሚያስችል ስፋቱ ቢያንስ ሃያ ሜትር በሃያ ሜትር ወለሉ ከስሚንቶ የተሠራ መጋዘን ያለው፣
3) የቡና ገለባውን ወደ ተለያዩ ምርቶች ለማቀነባባር የሚችል ማሽን ያለው፣
4) በማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪው ለሚሠሩ ሰራተኞች ለሥራው የሚያገለግል ተስማሚ የሥራ ልብስ ያዘጋጀ፣
5) ከማበጠሪያ ኢንዱስትሪዉ የሚወጣዉ ቆሻሻ አከባቢዉን እንዳይበክል የማስወገጃ ሥርዓት ያለዉ፣
6) የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ ያለው፣

## 2.11 የቡና ቅጠል ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ የቴክኒክ መስፈርት

የቡና ቅጠል ለተለያዩ አገልግሎቶች ለማቀነባበር የሚያስፈልገው የማቀነባባሪያና የምርት ማደራጃ ቦታ ሊኖረው ይገባል፤

1) የቡና ቅጠል ለተለያዩ አገልግሎቶች ለማቀነባበር ሚያስፈልገው የማቀነባባሪያና የምርት ማደራጃ ቦታ ያለው፤
2) የቡና ቅጠል ማከማቸት የሚያስችል ስፋቱ ቢያንስ ሃያ ሜትር በሃያ ሜትር ወለሉ ከስሚንቶ የተሠራ መጋዘን ያለው፤
3) የቡና ቅጠል ወደ ተለያዩ ምርቶች ለማቀነባባር የሚችል ማሽን ያለው፣
4) በማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪው ለሚሠሩ ሰራተኞች ለሥራው የሚያገለግል ተስማሚ የሥራ ልብስ ያዘጋጀ፣
5) ከማዘጋጃ ኢንዱስትሪዉ የሚወጣዉ ቆሻሻ አከባቢዉን እንዳይበክል የማስወገጃ ሥርዓት ያለዉ፣
6) የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ ያለው፣



እዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

## ክፍል ሦስት

## የቡና አዘገጃጀት ቴክኒክ

### 3.1 የአቅርቦት ቡና አዘገጃጀት ቴክኒክ

### 3.1.1 የታጠበ ቡና አዘገጃጀት ቴክኒክ

የታጠበ ቡና ለማዘጋጀት የሚከተሉትን የቴክኒክ መስፈርቶችን መከተል አለበት፡-

1) ቀይ እሸት ቡና ሲለቀም ቀይ ሆኖ ብስለቱን የጨረሰና ወጥ መልክ የያዘ መሆን አለበት፣
2) ክብደት ለመጨመር ሆን ተብሎ በተለቀመ እሸት ቡና ላይ ውሃ መርከፍከፍ የለበትም፣
3) ቡናው ንፅህናው በተረጋገጠ፣ የኬሚካል ንክኪ በሌለውና በተፈቀደ የቡና መያዣ መያዝና መጓጓዝ አለበት፣
4) የበሰለ፣ ያልበሰለ እና ብስለት የተላለፈውን ቡና በአንድነት ደባልቆ መሰብሰብ ወይም መሸምጠጥ የለበትም፣
5) ቀይ እሸት ቡና ከእንጨት ስብርባሪ፣ ከዋንዛ ፍሬ፣ ከአፈርና ከድንጋይ እንዲሁም ማናቸውም የቡናን ጥራት ሊያጓድሉ ከሚችሉ ነገሮች የፀዳ መሆን አለበት፣
6) ቡናው ወደ መፈልፈያ ቋት ከመግባቱ በፊት ለታጠበ ቡና ዝግጅት የማይመጥኑ ቡናዎች በመፈተሻ ጠረጴዛ (Sorting Table) መለየት አለባቸው፣
7) የተፈለፈሉ ቡናዎች በየዓይነታቸው /በየክብደታቸው/ ተለያይተው በውሃ እየተገፉ የሚገባቸውን አቅጣጫ በመያዝ ወደ ማቡኪያ ገንዳ ውስጥ በየደረጃቸው ለየብቻ እንዲገቡ መደረግ አለበት፣
8) ተፈልፍሎ በማቡኪያ ገንዳ የገባ ቡና ስኳራማ ማላጊው (Mucilage) እንዲለቅ ለማድረግ ቀዝቃዛ የአየር ንብረት ላለው አካባቢ ከ36 ሰዓታት ሳላነሰ ጊዜ፣ ሞቃታማ በሆነ አካባቢ ከ24 ሰዓት ሳላነሠ ጊዜ በገንዳ ውስጥ ውሃውን እየቀየሩ በማገላበጥ መቆየት ይኖርበታል፣ ሆኖም ግን የቡኬት ፍጥነቱ እንደየአከባቢዉ ስለሚለያይ ዘወትር ጠዋት ጠዋት በእጅ እየታሸ ቡኬቱን መጨረስ አለመጨረሱን መረጋገጥ ይኖርበታል።
9) በገንዳ ውስጥ እንዲቦካ የተደረገው ቡና መቡካቱ ከተረጋገጠ ወደ መጨረሻ ማጠቢያ ቦይ እንዲለቀቅ በማድረግ ከእንጨት በተሠራ መግፊያ እየታሸ በቡናው ላይ የቀረ ልጋግ ካለ እንዲለቅ በማድረግ ከእጥበቱ የሚወጣው ውሃ ንፁህ እስከሚሆን በማጠብ ቡናው ወደ መዘፍዘፊያ ገንዳ እንዲገባ መደረግ ይኖርበታል፣
10) በማጠቢያ ቦይ ላይ በሚገባ የታጠበ ቡና በመዘፍዘፊያ ገንዳ ውስጥ ከ16 እስከ 20 ሰዓት ያህል ውኃው ሣይቀያየር መቆየት አለበት። ሆኖም ግን የማድረቂያ አልጋ እጥረት ሲያጋጥም ውሃውን በየ24 ሰዓት እየቀየሩ፣ ለ48 ሰዓታት ማቆየት ይቻላል፣
11) ከመዘፍዘፊያ ገንዳ የወጣ ቡና ከወንፊት ሽቦ በተሰራ የማጠንፈፊያ አልጋ ላይ በማስጣት ውሃው እንዲንጠፈጠፍ በማድረግ አንዳንድ ያልተፈለፈሉና በፍልፈላ ወቅት በማሽን የተጎዱ ፍሬዎችን እየለቀሙ በማውጣት በማለዳ ጸሀይ የመጀመሪያ ድርቀት መከናወን አለበት፣



እዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

12) የመጀመሪያ ደረጃ አደራረቅ ጊዜውን የጨረሰ ቡና በፀሐይ ሙቀት ወይም በሰው ሰራሽ ዘዴ እንዲደርቅ መደረግ አለበት ሆኖም ግን የፀሐይ ሙቀት የቡናውን ሽፋን ስለሚሰነጣጥቀውና በቡናው ፍሬ ላይ ጉዳትን ስለሚያስከትል ጠዋት ከ3 እስከ 5 ሰዓት እና ከቀትር በኋላ ከ9 እስከ 11 ሰዓት በማስጣጣት መድረቅ አለበት፣

13) የመጨረሻ አደራረቅ አልጋ እና ከቃጫ የተሠራ ከማንኛውም ኬሚካል ቅሪት ነፃ የሆነ ብትን ጆንያና ዝርግ ፕላስቲክ በመጠቀም መከናወን አለበት፣

14) ያልተስተካከለ ድርቀት እንዳይኖር ማድረቂያ አልጋዎቹ ሽቦ በሚገባ መወጠር ይኖርበታል፣

15) ድርቀቱን የጨረሰ የታጠበ ቡና ወደ መጋዘን እንዲገባ ከመደረጉ በፊት የእርጥበት ይዘቱ ከ11.5% እስከ 12% መሆኑ መረጋገጥ አለበት፣

16) ደርቆ ወደ መጋዘን የገባ ቡና ከቃጫ የተሠራ ጆንያ ተሞልቶ አፉ ሣይሰፋ በማቆም ቢያንስ ለ24 ሰዓታት አየር በሚተላለፍበትና ንፅህናው በተጠበቀ መጋዘን ውስጥ መቆየት አለበት፣

17) እንዲናፈስ በጆንያ ክፍቱን ቆይቶ በመጋዘን የቆየውን ቡና የጆንያውን አፍ በመስፋት ከጣውላ ወይም ፕላስቲክ በተሰራ ርብራብ (Wooden Pallet or plastic) ላይ እንዲደረደር መደረግ አለበት፣

18) በአግባቡ ታጥቦና ደርቆ ለገበያ የሚቀርብ የታጠበ ቡና በ60 ኪሎ ግራም መጠን ተለክቶ በቃጫ ጆንያ መያዣ መከማቸት/መጫን አለበት፣

19) ቡናው የሚዘጋጀው በdemucilager ከሆነ ከ "8 እስከ 12" ከተዘረዘሩት ውጭ እሸት ቡናው በሚፈለፈልበት ወቅት ልጋጉ በማሽኑ እንዲለቅ ስለሚደረግ ቡናው ከተፈለፈለ በኋላ ክብደት ያለው ቡና መቡካት ሳያስፈልገው በውሃ እየተገፋ ወደ መዘፍዘፊያ ገንዳ እንዲገባና ከ8 ሰዓት ላላነሰ ጊዜ እንዲቆይ ከተደረገ በኋላ ወጥቶ ከ 9 እስከ 18 የተዘረዘሩ ሂደቶችን ማለፍ ይኖርበታል፡፡

### 3.1.2 ያልታጠበ /ተፈጥሯዊ/ ቡና አዘገጃጀት ቴክኒክ

ያልታጠበ/ተፈጥሯዊ/ ቡና ለማዘጋጀት የሚከተሉትን የቴክኒክ መስፈርቶችን መከተል አለበት፡-

1) በአግባቡ የተለቀመ ቀይ እሸት ቡናን ብቻ መጠቀም አለበት፣

2) የተለቀመ ቀይ እሸት ቡና የሚደርቀው ከመሬት ዜሮ ነጥብ ስምንት እስከ አንድ ሜትር ከፍታ ባለውና ከአካባቢ ከሚገኝ ቁሳቁስ ወይም ከሽቦ በተሠራ አልጋ ወይም ከሲሚንቶ በተሠራ አውድማ ላይ ነው፣

3) ቡናው በተስተካከለ ሁኔታ ወይም ዘርዘር ብሎ እንዲደርቅ ቡናው ከ3-5 ሣንቲ ሜትር ባልበለጠ ውፍረት መስጣት አለበት፣

4) አየሩ ደመናማና ቀዝቃዛ በሚሆንበት ጊዜ የተሰጣው ጀንፈል ቡና ተሰብስቦ በዝርግ ጆንያና በፕላስትክ መሸፈን ይኖርበታል፣

5) አግባብነት ባለው የፌዴራል ወይም የክልል አካል በተመሠከረለት የእርጥበት መለኪያ መሣሪያ ትክክለኛው የተዘጋጀ የጀንፈል ቡና የእርጥበት መጠን (12%) መብለጥ የለበትም፣

6) ከላይ በተራ ቁጥር 5 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የቡናው እርጥበት ከ12% በላይ ከሆነ ትክክለኛውን የድርቀት መጠን እስከሚይዝ ከስሚንቶ በተሰራና በጸዳ አውድማ ላይ ወይም ለዚህ ሥራ በተዘጋጀው አልጋ ላይ ማድረቅ ይኖርበታል፣



እዱኛ ደበላ ቡቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

7) ቡናው ንፅህናው በተረጋገጠ፣ የኬሚካል ንክኪ በሌለውና በተፈቀደ የቡና መያዣ መከማቸትና መጓጓዝ አለበት፣

8) ለጀንፈል ዝግጅት የሚቀርብ ቡና ከእንጨት ስብርባሪ፣ ከዋንዛ ፍሬ፣ ከአፈርና ከድንጋይ እንዲሁም ማናቸውም የቡናን ጥራት ሊያጓድሉ ከሚችሉ ነገሮች የፀዳ መሆን አለበት፣

9) ወደ ግብይት የሚቀርብ ጀንፈል ቡና በፕላስቲክ ከረጢት፣በማዳበሪያ ከረጢት ወይም ለቡና ባልተፈቀደ መያዣ መከማቸት/መጫን የለበትም፣

10) ጀንፈል ቡናን ለመቀሸርና ያልታጠበ ቡና ለማዘጋጀት ወደ መቀሸሪያ ማሽን ገብቶ ገለባውና ፍሬው መለየት አለበት፣

11) በጀንፈል ቡና መቀሸሪያ ማሽን የተለየው ያልታጠበ ቡና እና ገለባው ተለይቶ በአግባቡ በሚፈለግበት ቦታ መከማቸት አለበት፣

12) ጀንፈል ቡናው ተበጥሮ ከገለባው ከተለየ በኋላ በካታዶር የማይወጡ ወይም ያልተወገዱ ጉድለቶች ለቡና መልቀሚያ በተዘጋጀ ጠረጴዛ ላይ መለቀም ይኖርባቸዋል፣

13) በአግባቡ ተበጥሮ ለገበያ የሚቀርብ ያልታጠበ ቡና በ85 ኪሎ ግራም መጠን ተለክቶ በቃጫ ጆንያ መያዣ መከማቸት/መጫን አለበት፣

14) ቡና በሚዘጋጅበት/በሚበጠርበት ወቅት የማበጠሪያ መሣሪያው አገጣጠም (adjustment) እንደ ቡናው የፍሬ መጠን የተስተካከለ መሆን ይኖርበታል፣

## 3.2 የወጪ ገበያ ቡና አዘገጃጀት ቴክኒክ

### 3.2.1 የወጪ ገበያ የጥሬ ቡና አዘገጃጀት

የወጪ ገበያ ቡና ለማዘጋጀት የሚከተሉትን የቴክኒክ መስፈርቶችን መከተል ያስፈልጋል፡

1) የአቅርቦት ቡና ወደማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪው እንደደረሰ በምርት አይነት፣ ደረጃ፣ መጠን፣ ባለቤት ገላጭ በሆነ እና ለቆጠራ በሚያመች መልኩ ተደርድሮ መከማቸት አለበት፣

2) በተለያየ ደረጃ የተከማቸውን ቡና ለኤክስፖርት ለማዘጋጀት የዝግጅት ምጣኔ ተሰርቶ ወደ ቋቱ ይገባል፣

3) የጠቆሩ፣ የገረጡና በሻጋታ የበለዙ፣ የተሰባበሩ የቡና ፍሬዎች እና ሌሎች የባዕድ አካላት በኤሌክትሮኒክ መለያ መሳሪያ (Uv light) ወይም በቀለም መለያ /Color sorter) ወይም በሰው ኃይል ይለያሉ፣

4) ለዚሁ አገልግሎት ብቻ የተዘጋጀ አዲስ የቃጫ ጆንያ ላይ አስፈላጊ መረጃዎች (Labeling) በማተም የተዘጋጀ ቡና በ60 ኪሎ ግራም ተመዝኖ ይታሸጋል፣

5) ከላይ በተራ ቁጥር 4 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ብትን ቡና በኮንቴነር ከሆነ ለዚሁ ተግባር ተዘጋጅቶ በቀረበው ኮንቴነር ከ18 ቶን እስከ 19.20 ቶን ብትን ቡና መሞላት ይኖርበታል፤

6) የተዘጋጁ ቡናዎችን ወደ ውጭ እስከሚልክ ድረስ ባዕድ ከሆኑ ቅባቶች፣ ኬሚካሎች፣ ቆዳ፣ ነዳጅ፣ ሽታ የሚያመጡ የእህል፣ የምግብ ወይንም የመጠጥ ዓይነቶች ጋር ንክኪ በማይፈጥሩበት ሁኔታ ማከማቸት አለበት



አዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

### 3.2.2 የተቆላ ወይም ተቆልቶ የተፈጨ የወጪ ቡና አዘገጃጀት ቴክኒክ

የተቆላ ወይም ተቆልቶ የተፈጨ የወጪ ቡና ለማዘጋጀት የሚከተሉትን የቴክኒክ መስፈርቶችን መከተል ያስፈልጋል፡-

1) ማንኛውም ለተቆላ ወይም ተቆልቶ ለተፈጨ ቡና ዝግጅት የሚውል ጥሬ ቡና በዚህ መመሪያ መሰረት የአቅርቦት ወይም የወጪ ገበያ ቡና ዝግጅት ቴክኒክ ያጠናቀቀ መሆን አለበት፣
2) ጥሬው ቡና ወደመቁያው ማሽን/ምድጃ ገብቶ በቀላል፣መካከለኛ እና በደማቅ ጥቁር ይቆላል፣
3) የተቆላው ቡና ከመቁያው ማሽን ወጥቶ ይቀዘቅዛል፣
4) ተቆልቶ የቀዘቀዘው ቡና የሚፈጭ ከሆነ ለዚህ አገልግሎት በተዘጋጀው የቡና መፍጫ ይፈጫል፣
5) ተቆልቶ የቀዘቀዘው ወይም የተፈጨ ቡና በተዘጋጀው ማሸጊያ የቡናው አይነት፣ መጠን፣ የጥራት ደረጃ፣ የምርት ዘመን፣ የመጠቀሚያ ጊዜ፣ ታትሞ ይታሸጋል፣
6) የተዘጋጀው ቡና ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ በአግባቡ መከማቸት ይኖርበታል፣

## 3.3 የቡና ገለባና ቅጠል አዘገጃጀት ቴክኒክ

### 3.3.1 የቡና ገለባ አዘጋጃጀት

የቡና ገለባን ለማዘጋጀት የሚከተሉትን የቴክኒክ መስፈርቶችን መከተል ያስፈልጋል፡-

1) በአንቀጽ 4.2. የተጠቀሰው አዘገጃጀት ቴክኒነክ መሠርት የጀንፈል ቡና በመቀሸሪያ ማሽን ገብቶ ሲቀሸር ከዋናው የቡና ፍሬ የተለየውን ገለባ ማደራጀት፣
2) ጀንፈል ቡና ሲቀሸር የሚወጣው ገለባው በውስጡ ከአንድ በመቶ በላይ ንጽህ ቡና እንዳይኖር መዘጋጀት አለበት፤
3) የታጠበ ቡና ከነገለፈቱ በማሽኑ ሲፈለፈል የተለየው ገለፈት ተለይቶ በአግባቡ በሚፈለግበት ቦታ መከማቸት፣ ለሚፈለግበት አገልግሎት እንዲውል ማደራጀት፣
4) በአግባቡ የተደረጃውን የጀንፈል ቡና ገለባ ወይም የታጠበ ቡና ገለፈት ለገበያ በሚቀርብ ሁኔታ በጆንያ ወይም በሌላ ተስማሚ ማሸጊያ አሸጎ እንዲከማች ወይም እንዲጓጓዝ ማድረግ፤

### 3.3.2 የቡና ቅጠል አዘጋጃጀት

የቡና ቅጠል ለማዘጋጀት የሚከተሉትን የቴክኒክ መስፈርቶችን መከተል ያስፈልጋል፡-

1) የቡና ተክል ፍሬ ከሰጠ በኃላ አገልገሎቱን ያጠናቀቀ ቅጠል ሲራገፍ ወይም ሊራገፍ የደረሰውን ቅጠል ከቡና ማሳ ለቅሞ መሰብሰብ፣
2) ከማሳው የተሰበሰበውን የቡና ቅጠል ከቡና ቅጠል ውጭ የሆኑትን ባዕድ አካላትን በመለየትና በማደራጀት በንጹህ ቦታ ማከማቸት፣
3) ለገበያ የሚዘጋጀው የቡና ቅጠል የበሰበሰ፣ ከአፈር ጋር የታሸና የሻገተ መሆን የለበትም፣
4) በአግባቡ የተደረጃውን  የቡና ቅጠል ለገበያ በሚቀርብ ሁኔታ በጆንያ ወይም በሌላ ተስማሚ ማሸጊያ አሸጎ እንዲከማች ወይም እንዲጓጓዝ ማድረግ ያስፈልጋል::

### 3.4 የልዩ ቡና ዝግጅት የቴክኒክ መሥፈርት

የልዩ ቡና አዘገጃጀት የቴክኒክ መሠፈርት በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 3.2 እና 3.3 የተመለከቱትን የአቅርቦት ቡና እና የወጪ ቡና አዘገጃጀት የቴክኒክ መስፈርት ሙሉ በሙሉ ያማላ ሆኖ፡-

1) በተስማሚ መሬት በተፈላጊ የቡና ዝርያ የለማውን ቀይ እሸት ቡና በተፈላጊ የብስለት ወቅት በጥንቃቄ ቀይ ቀዩን ብቻ መልቀም፣
2) ለታጠበ ቡና ዝግጅት ከሆነ ከተለቀመ እስከ 8 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ወደ ኢንደስትሪው ለዝግጅት መግባት አለበት፣
3) ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ የተለቀመውን ቀይ እሸት ቡና ንጽህናውን በጠበቀ ማድረቂያ በተስተካከለ የፀሐይ በጥንቃቄ 11.5 እስከ 12 በመቶ እርጥበት መጠን ያለው ጀንፈል ቡና ተዘጋጅቶ ወደ መቀሸሪያ ኢንዱስትሪ ለዝግጅት መግባት አለበት፤
4) የታጠበ ቡናም ሆነ ያልታጠበ ቡና በአዲስ ጆንያ ወይም ሌላ የተፈቀደ ማሸጊያ መግባት አለበት፣
5) በቡና ጣዕምና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ የታጠበ ቡና ደረጃ 1 እና 2፣ ያልታጠበ ቡና ደረጃ 1 እና 2 ማግኘት ይጠበቃል።
6) አጠቃላይ የቡና ጣዕምና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ውጤት ከ80 በመቶ በላይ ሊሆን ይገባል።

## ክፍል አራት

## የቡና ጥራትና ጣዕም ምርመራ አሠራር

### 4.1 የእሸትና ጀንፈል ቡና ጥራት ምርመራ

1) የቀይ እሸት የጥራት ምርመራ በዋናነት ያልበሰለ አረንጓዴ፣ ብስለት የተላለፈው፣ የባዕድ ሽታ ያለበት፣ የተለያዬ መጠን ያለው የቡና ፍሬዎች የተቀላቀሉበት፣ መሬት ላይ ወድቆ የቆየ ቡና ተለቅሞ የተቀላቀለበት፣ በበሽታና በተባይ የተጎዳ ፍሬ፣ ተለቅሞ ያደረ እና በፀሐይ ብርሃን ተጋልጦ የቆየ እና ቡኪት የጀመረ ፍሬ፣ የቡና ቅጠልና ቅርንጫፍ እንዲሁም ሌሎች ባዕድ ነገሮች ያልተቀላቀሉበት መሆኑን ይለያል፣
2) የጀንፈል ቡና የጥራት ምርመራ በዋናነት ያልበሰለ አረንጓዴ የቡና ፍሬ፣ ብስለት የተላለፈው የቡና ፍሬ ሻጋታ የሌለበት፣ ባዕድ ሽታ የሌለው፣ መልሶ ያልረጠበ፣ የተለያዬ መጠን ያልሆነ ጀንፈል ያልተቀላቀለበት/ የዝርያ መቀላቀል/፣ በውሃ ያልረጠበ፣ በአፈር ያልታሸ፣ ባዕድ ነገሮች ያልተቀላቀሉበት (ዲንጋይ፣ የዘፍ ፍሬ፣ ብረታ ብረት፣ አፈር…)፣ በበሽታና በተባይ ያልተጎዳ፣ የተስተካከለ አደራረቅ ያለው መሆኑን ይለያል፣

### 4.2 የአቅርቦት ቡና ጥራት ምርመራ

#### 4.2.1 በወረዳ ደረጃ የሚደረግ ጥራት ምርመራ

1) የታጠበ ቡና አዘገጃጀት በ3.1.1 እና ያልታጠበ ቡና አዘገጃጀት 3.1.2 የተዘረዘሩትን የአዘገጃጀት ቴክኒክ መሥፈርት መሠረት መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣



ጁዱኛ ደበላ ቦቴ (ኢንጅ ዶ)

2) የተዘጋጀው ቡና ንፅህናው በተጠበቀና ለቡና መጫኛ አገልግሎት ልዩ ምልክት ባለው ጆንያ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፣

3) ቡና በሚያጓጉዙበት ወቅት የቡናን ጥራት ሊያጓድሉ ከሚችሉ ነገሮች ጋር መጫን የለበትም፣

4) የታጠበም ሆነ ያልታጠበ ቡና የጥራት ምርመራ ለማድረግ ከአንድ መኪና ግማሽ ኪሎ ግራም/500 ግራም/ የሚመስስ ናሙና ተወስዶ የእርጥበት፣ የእይታና ሽታ ልየታ ይደረግበታል።

5) የአቅርቦት ቡና ከመሸኘቱ በፊት የእርጥበት ደረጃ 11.5 እስከ 12 በመቶ መሆኑ በእርጥበት መለኪያ መሣሪያ መረጋገጥ አለበት።

### 4.2.2 የቡና ጥራትና ጣዕም ምርመራ አሠራር

ማንኛውም ቡና ለጥራትና ጣዕም ምርመራ ሲቀርብ፡-

1) በተሰጠው የቡና መሸኛ ወይም የዝግጅት ሰርተፊኬት መሠረት የመጣበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ የተዘጋጀበት ኢንዱስትሪ፣ የቡናው ዝግጅት ዓይነት፣ የመኪናው ሠሌዳ ቁጥር፣ የቡናው ባለቤት ስም፣ የሹፌሩ ስም፣ የደረሰበት ቀን፣ በማዕከሉ ይመዘገባል፣

2) የቀረበው ቡና የተሸኘበትና የደረሰበት ጊዜ ተረጋግጦ በናሙና ማውጫ ካርድ ላይ ቀን፣ የተመራበት ተራ ቁጥር፣ ቡናውን የጫነው መኪና ሠሌዳ ቁጥር፣ የቡናው ኪሻ መጠን፣ የአቅርቦት ቡና ከሆነ የፕሎምብ ቁጥር ተመዝግቦ ለናሙና አውጪ ይመራል፣

3) ናሙና አውጪው በናሙና ማውጫ ካርድ መሰረት ከቀረበው በየ አስር ሺህ ኪሎ ግራም ቡና አንድ ኪሎ ግራም ወካይ ናሙና በመውሰድ ስሙን ጽፎና ፈርሞ ካርዱን ናሙና በተወሰደበት ከረጢት ውስጥ በመክተት ለኮድ ክፍል ያስረክባል፣

4) ናሙና አውጪው በናሙና ማውጫ ካርድ መሠረት በጆንያ ወይም በብትን በኮንቴነር የሚቀርበውን ቡና ቅድመ ምርመራ ከቀረበው ከአስራ ስምንት ሺህ ኪሎ ግራም እስከ አስራ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ኪሎ ግራም ቡና አንድ ኪሎ ግራም ወካይ ናሙና በመውሰድ ስሙን ጽፎና ፈርሞ ካርዱን ናሙና በተወሰደበት ከረጢት ውስጥ በመክተት ለኮድ ክፍል ያስረክባል፣ይህንኑ ለኤክስፖርት ጭነት ወደ ኮንቴነሩ ሲጋባ ድጋሚ ወይም ለማመሳከሪያነት አንድ ኪሎ ግራም ቡና ይወሰዳል።

5) የኮድ ክፍሉ የቡናው ባለቤት ስም፣ የመኪናው ሠሌዳ ቁጥርና የቡናው ኪሻ ብዛት ሳይጠቀስ የዕለት ኮድ ይሰጣል፣

6) ናሙናው ኮድ ከተሰጠው በኋላ ቡናው የመጣበትን ክልል፣ ዞንና ወረዳ የኮድ ቁጥርና ቀን መረጃ የያዘ አነስተኛ ካርድ በማዘጋጀት ወካይ ናሙናውን በያዘው ከረጢት ውስጥ በማስገባት ወደናሙና ዝግጅት ክፍል ይተላለፋል፣

7) የናሙና ዝግጅት ክፍሉ ቡናን በጥሬና በተቆላ መልክ እንዲሁም ለማመሳከሪያነት የሚውለውን በተለየ መልክ ለምርመራ ያቀርባል፣

8) የምርመራ ክፍሉ የቀረበለትን ናሙና የጥሬና የጣዕም ምርመራ በማድረግ የቡናውን ጥራትና ደረጃ የሚያሳይ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣



እዱኛ ደበላ ቡቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

## ክፍል አምስት

## ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

### 5.1 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

በደንቡ ክፍል አራት ንዑስ አንቀጽ ክፍል አንድና ንዑስ ክፍል ሁለት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት፡-

1) በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል አመልካቾች እንዲሞሉት የተዘጋጀውን ቅጽ (በዚህ መመሪያ እዝል 1 የተመለከተውን) ሞልቶ ማቅረብ አለበት፣
2) ከተሞላው ቅጽ ጋር በደንቡ እና በዚህ መመሪያ የተገለጹትን መስፈርቶች ስለሟሟላቱ የሚያሳዩ ማስረጃዎችን አያይዞ ማቅረብ አለበት፣
3) በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው የሥራ ኃላፊ የቀረበውን ማግልከቻ ተቀብሎ የውሳኔ ሃሳብ እንዲያቀርብ ለሚመለከተው ባለሙያ ይመራል፡፡
4) ከላይ በተራቁጥር 5.1.3 የተመራለት ባለሙያ አመልካቹ ያቀረባቸውን ሰነዶች በቴክኒክ መስፈርቱ መሠረት መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤ በአካል በመስክ ተገኝቶ ማረጋገጥ ሲያስፈልገው ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡ የማጠቃለያ የግመገማ ቅጽ ሞልቶ ለሥራ ኃላፊው ለውሳኔ ያቀርባል፡፡
5) የሥራ ኃላፊው የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ በመመልከት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡ ነገር ግን ባለሙያው ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚሟላ የቴክኒክ መሥፈርት ጉድለት ያለው ከሆነ ለአመልካቹ በአምስት የሥራ ቀናት እንዲያሟላ እድል ይሰጣል፡፡
6) በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጠው የሥራ ኃላፊ ማመልከቻውን ውድቅ ካደረገ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የክልከላውን ምክንያት ተጠቅሶ ላመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፣
7) አመልካቹ በብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ሰጪ ክፍሉ የተሰጠውን ውሳኔ የሚቃወም ከሆነ ቅሬታውን በጽሁፍ ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል የበላይ ኃላፊ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይችላል፣
8) የባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል የበላይ ኃላፊ የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣
9) ቅሬታ አቅራቢው ባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የበላይ ኃላፊ በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማማ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት በስልሳ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ማመልከት ይችላል፡፡



እዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

## 5.2 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

### 5.2.1 የአነስተኛ ቡና አምራች አርሶ አደር የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ

አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው የቡና አምራች አርሶ አደሮች የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፣

1) አርሶ አደር ስለመሆኑ የመሬት ይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ በሚመለከተው የክልል የመንግሥት አካል የተሰጠ ማረጋገጫ ካርታ ማቅረብ የሚችል፣
2) የለማና ምርት የሚሰጥ የቡና ማሳ መጠን ከ2 ሄክታር እና ከዚያ በላይ ስለመሆኑ በክልል በባለስልጣኑ ወይም ስልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፣
3) በምርት ዘመኑ በማሳው የተመረተ የቡና ምርት መጠን ግምት አግባብ ካለው ክልል አካል የተሰጠ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፣
4) ቡናውን ለማጠብ ወይም ለመቀሸር የራሱ አነስተኛ ማዘጋጃ ማሽን ወይም ኢንዱስትሪ ወይም ከህጋዊ ሶስተኛ ወገን የማጠቢያ ወይም መቀሸሪያ ኢንዱስትሪ የአገልግሎት ኪራይ ውል ስምምነት ማቅረብ የሚችል፣ወይም ቡናዉን ለኤክስፖርት ሲያዘጋጅ ከህጋዊ ሶስተኛ ወገን የማጠቢያ ወይም መቀሸሪያ ኢንዱስትሪ የአገልግሎት ኪራይ ውል ስምምነት ማቅረብ የሚችል መሆኑ አግባብ ካለዉ የክልል አካል መረጃ ሚያቀርብ ከሆነ፣

### 5.2.2 የቡና አምራች የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር/ዩኒየን የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ

የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1) በአንቀጽ 2.1 እና/ወይም 2.2 እና 2.3 ላይ የተጠቀሱትን የቴክኒክ መስፈርቶች የሚያሟላ የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለዉ ስለመሆኑ የባለቤት ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል እና የኢንዱስትሪ የብቃት ማረጋገጫ የሚያቀርብ፣
2) በመንግስት አካል የተረጋገጠ የመመስረቻ እና መተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም ህጋዊ ሰዉነት ያገኘበትን ማስረጃ ማቅረብ፤
3) ቡና አምራች ገበሬዎች የህብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኑ የቦርድ ሰብሳቢ/ ዋና ሥራአስኪያጅ የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል፣
4) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2.5 ተቁጥር 1 ሀ ላይ የተቀመጡትን የቢሮ እና በተራቁጥር 2 ሀ፣ለ፣ሐ፣መ እና ሠ የተመለከቱትን የሰው ኃይል መስፈርቶችን ያሟላ፤

### 5.2.3 የቡና አልሚ ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ

የቡና አልሚ ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠዉ አመልካቹ፡-

1) ያመረተውን ምርት ለማጠብ ወይም ለማበጠር የሚያስችል የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለው ስለመሆኑ ማሳረጃ አግባብ ካለው የክልል አካል የሚያቀርብ፤
2) በአንቀጽ 2.3 ላይ የተጠቀሱትን የቴክኒክ መስፈርቶች የሚያሟላ የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለዉ ስለመሆኑ የባለቤት ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል እና የኢንዱስትሪ የብቃት ማረጋገጫ የሚያቀርብ፣



እዱኛ ደበላ ቦቴ
ዋና ዳይሬክተር

3) የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል፣
4) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሰርተፍኬት የማቅረብ፣
5) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2.5 ተቁጥር 1 ሀ ላይ የተቀመጡትን የቢሮ እና በተራቁጥር 2 ሀ፣ለ፣ሐ፣መ እና ሠ የተመለከቱትን የሰው ኃይል መስፈርቶችን ያሟላ፣
6) የአከባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሪፖርት የሚያቀርብ፣
7) ከፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ከወንጀል ነጻ ስለመሆኑ የጣት አሻራ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣ የብቃት ማረጋገጫ ጠያቂው አክሲዮን ማህበር ከሆነ የማህበሩ ሊቀ መንበር የጣት አሻራ እና የተመረጠበትን የጠቅላላ ጉባኤ ቃሌ ጉባኤ የሚያቀርብ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

### 5.2.4 የቡና አቅራቢነት የብቃት ማረጋገጫ

የቡና አቅራቢነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፤

1) በአንቀጽ 2.1 ወይም 2.2 ላይ የተጠቀሱትን የቴክኒክ መስፈርቶች የሚያሟላ የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለዉ ስለመሆኑ የባለቤት ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል እና የኢንዱስትሪ የብቃት ማረጋገጫ የሚያቀርብ፣
2) አግባብ ባለው የመንግስት አካል የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል መሰረት ከሶስተኛ ወገን ያገኘዉ ሚዛንና የእርጥበት መቆጣጠሪያ መሳሪያ ያሉት ከሆነ
3) ቢያንስ 500,000 (ግማሽ ሚሊዮን ብር) በባንክ የተረጋገጠ ካፒታል ማስረጃ የሚያቀርብ፣
4) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2.5 ተራ ቁጥር 1 ሀ ላይ የተቀመጡትን የቢሮ እና በተራቁጥር 2 ሀ፣ለ፣ሐ፣መ እና ሠ የተመለከቱትን የሰው ኃይል መስፈርቶችን ያሟላ፣መሆን አለበት፡፡

### 5.2.5 የቡና አቅራቢ ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ

የቡና አቅራቢ ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጠው አመልካቹ፡-

1) በዚህ መመሪያ ለአቅራቢነት የተቀመጡ መስፈርቶችን አሟልቶ የብቃት ማረጋገጫ እና የንግድ ፈቃድ ያገኘ
2) በአንቀጽ 2.3 ላይ የተጠቀሱትን የቴክኒክ መስፈርቶች የሚያሟላ የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለዉ ስለመሆኑ የባለቤት ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል እና የኢንዱስትሪ የብቃት ማረጋገጫ የሚያቀርብ፣
3) ከአምራች አርሶአደሮች ጋር የእሸትና ጀንፈል ቡና ግዢ ውል ፈጽሞ በውሉ መሠረት ለመክፈል የተስማማ፣
4) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2.5 ተቁጥር 1 ሀ ላይ የተቀመጡትን የቢሮ እና በተራ ቁጥር 2 ሀ፣ለ፣ሐ፣መ እና ሠ የተመለከቱትን የሰው ኃይል መስፈርቶችን ያሟላ፣
5) የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል እና
6) የግብር ከፋይ መለየ ቁጥር ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፡፡

### 5.2.6 የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠዉ አመልካቹ፡-



እዱኛ ደበላ ቦቴ
ዋና ዳይሬክተር

1) በአንቀጽ 2.3 ላይ የተጠቀሱትን የቴክኒክ መስፈርቶች የሚያሟላ የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለዉ ስለመሆኑ የባለቤት ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል እና የኢንዱስትሪ የብቃት ማረጋገጫ የሚያቀርብ፣
2) ለግል አመልካች ለሥራው የሚያስፈልግ ቢያንስ 1,000,000 (አንድ ሚሊየን) እና የአንድ ዓመት የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሚያሳይ ከሚመለከተው ባንክ የተረጋገጠ የሰነድ ማስረጃ የሚያቀረብ፣
3) ለአክሲዮን ማህበር ለሥራው የሚያስፈልግ 1,500,000 (አንድ ሚሊየን አምስት መቶ ሽህ) ብር በባንክ የተረጋገጠ ማስረጃ እና ከመስራቾቹ ቢያንስ ሁለት ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ያላቸው አባላት የአንድ ዓመት የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሚያሳይ ከሚመለከተው ባንክ የተረጋገጠ የሰነድ ማስረጃ የሚያቀርብ በተጨማሪም በሚመለከተው የመንግስት ተቋም የተረጋገጠ የመተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ጽሑፍ የሚያቀርብ፣
4) የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል፣
5) የግብር ከፋይ መለየ ቁጥር ማቅረብ የሚችል፣
6) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2.5 ተቁጥር 1 ሀ ላይ የተቀመጡትን የቢሮ እና በተራቁጥር 2 ሀ፣ለ፣ሐ፣መ እና ሠ የተመለከቱትን የሰው ኃይል መስፈርቶችን ያሟላ፣
7) ከፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ከወንጀል ነጻ ስለመሆኑ የጣት አሻራ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣ የብቃት ማረጋገጫ ጠያቂው አክሲዮን ማህበር ከሆነ የማህበሩ ሊቀ መንበር የጣት አሻራ እና የተመረጠበትን የጠቅላላ ጉባኤ ቃሌ ጉባኤ፣
8) የቋሚ ንብረት ማረጋገጫ ሰነድ ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም የሚያቀርብ፣የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን ወይም ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ያለው አባል ቋሚ ንብረት ማስረጃ የሚያቀርብ እና የዋና የሥራ አድራሻ ማረጋገጫ ሰነድ የሚያቀርብ
9) ነባር የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን ወይም አዲስ የተመሰረተ የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ አስተዳዳሪ ወይም ሊቀመንበር በማንኛውም ንግድ ወይም በማምረት ሥራ ወይም በሙያው ተሰማርቶ መልካም አፈጻፀምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፣
10) በማንኛውም ንግድ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ወይም በተሠማራበት የሙያ መስክ መልካም አፈጻጸምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል፤ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

### 5.2.7 የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ

የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ አገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1) በአንቀጽ 2.3 ላይ የተጠቀሱትን የቴክኒክ መስፈርቶች የሚያሟላ የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለዉ ስለመሆኑ የባለቤት ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል እና የኢንዱስትሪ የብቃት ማረጋገጫ የሚያቀርብ፣



እዱኛ ደበላ ቡቴ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

2) ወደ ኢንዱስትሪው ለአገልግሎት/ ቡናውን ለማዘጋጀት/ ለሚመጡ ሕጋዊ ተገልጋዮች ማስተናገጃ ግልጽ መመሪያ የሚያቀርብ፣
3) የደንበኞች ማስተናገጃ የወጪና የገቢ ሰነዶችና ለአስበጣሪዉ የሚሰጠዉ ሰረተፊኬት የሚያቀርብ
4) የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል፣
5) የግብር ከፋይ መለየ ቁጥር ማቅረብ የሚችል፣
6) የኢንዱስትሪ የግንባታ ፈቃድ የሚያቀርብ
7) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2.5 ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶችን ያሟላ፤
8) ከፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ከወንጀል ነጻ ስለመሆኑ የጣት አሻራ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣ የብቃት ማረጋገጫ ጠያቂው የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ ሊቀ መንበር የጣት አሻራ እና የተመረጠበትን የጠቅላላ ጉባኤ ቃሌ ጉባኤ የሚያቀርብ፣መሆን ይገባል፡፡

5.2.8 **የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ**

የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ አገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1) በአንቀጽ 2.1 ወይም 2.2 ላይ የተጠቀሱትን የቴክኒክ መስፈርቶች የሚያሟላ የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለዉ ስለመሆኑ የባለቤት ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል እና የኢንዱስትሪ የብቃት ማረጋገጫ የሚያቀርብ፣
2) ወደ ኢንዱስትሪው ለአገልግሎት/ ቡናውን ለማዘጋጀት/ ለሚመጡ ሕጋዊ ተገልጋዮች ማስተናገጃ ግልጽ መመሪያ የሚያቀርብ፣
3) የደንበኞች ማስተናገጃ የወጪና የገቢ ሰነዶችና ለአስበጣሪዉ የሚሰጠዉ ሰረተፊኬት የሚያቀርብ
4) የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል፣
5) የግብር ከፋይ መለየ ቁጥር ማቅረብ የሚችል፣
6) የኢንዱስትሪ የግንባታ ፈቃድ የሚያቀርብ፣
7) አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልኩ የተደራጀ አገልግሎት መስጫ ቢሮ ያለው፣
8) ከፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ከወንጀል ነጻ ስለመሆኑ የጣት አሻራ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣
9) የብቃት ማረጋገጫ ጠያቂው የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ ሊቀ መንበር የጣት አሻራ እና የተመረጠበትን የጠቅላላ ጉባኤ ቃሌ ጉባኤ የሚያቀርብ እና
10) ባለስልጣኑ ለአገልግሎት ሰጪዎች ያዘጋጀውን የግዴታ ውል መቀበሉን በፊርማ ያረጋገጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

5.2.9 **የቡና ጅምላ ነጋዴነት ብቃት ማረጋገጫ**

የቡና ጅምላ ንግድ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፤

1) ደረጃውን የጠበቀና የተመዘገበ ስፋቱ ከ100 ካሬ ሜትር ያላነሰ መጋዝን በራሱ ወይም በኪራይ ከሆነ ሕጋዊ የኪራይ ውል ማስረጃ ማቅረብ፣



እዱኛ ደበላ ቡቴ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

2) ለግል አመልካች ለሥራው የሚያስፈልግ ቢያንስ ብር 250,000 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ.ህ ብር) እና የአንድ ዓመት የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሚያሳይ ከሚመለከተው ባንክ የተረጋገጠ የሰነድ ማስረጃ የሚያቀረብ፣

3) የብቃት ማረጋገጫ ጠያቂው የንግድ ማህበር ከሆነ ለሥራው የሚያስፈልግ ብር 250,000 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ.ህ ብር) በባንክ የተረጋገጠ ማስረጃ እና ከመስራቾቹ ቢያንስ ሁለት ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ያላቸው አባላት የአንድ ዓመት የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሚያሳይ ከሚመለከተው ባንክ የተረጋገጠ የሰነድ ማስረጃ እና በሚመለከተው የመንግስት ተቋም የተረጋገጠ የመተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ጽሑፍ የሚያቀርብ፣

4) በሚመለከተው አካል የተመሰከረለት በባለቤትነት የተያዘ ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሦስተኛ ወገን የተገኘ ሚዛን ያለው፣

5) አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልኩ የተደራጀ አገልግሎት መስጫ ቢሮ ያለው መሆኑ፣

6) በድርጅቱ ስም የተሟላ ሠራተኛ በቋሚነት መቅጠሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣

7) የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል፣

8) የግብር ከፋይ መለየ ቁጥር ማቅረብ የሚችል፣

9) ከፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ከወንጀል ነጻ ስለመሆኑ የጣት አሻራ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣ የብቃት ማረጋገጫ ጠያቂው የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ ሊቀ መንበር የጣት አሻራ እና የተመረጠበትን የጠቅላላ ጉባኤ ቃለ ጉባኤ

10) የቋሚ ንብረት ማረጋገጫ ሰነድ ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም የሚያቀርብ፣የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን ወይም ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ያለው አባል ቋሚ ንብረት ማስረጃ የሚያቀርብ እና የዋና የሥራ አድራሻ ማረጋገጫ ሰነድ የሚያቀርብ እና

11) ነባር የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን አዲስ የተቋቋመ የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ አስተዳዳሪ ወይም ሊቀመንበር በማንኛውም ንግድ ወይም በማምረት ሥራ ወይም በሙያው ተሰማርቶ መልካም አፈጻፀምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

### 5.2.10 የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ቸርቻሪ ነጋዴነት ብቃት ማረጋገጫ

የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ቸርቻሪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው፣

1) የራሱ ወይም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው መደብር ስለመኖሩ ህጋዊ ማስረጃ የሚያቀርብ፣

2) በሚመለከተው አካል የተመሰከረለት በባለቤትነት የተያዘ ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሦስተኛ ወገን የተገኘ የጠረጴዛ ሚዛን ያለ መሆን ማስረጃ፣

3) የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል፣

4) የግብር ከፋይ መለየ ቁጥር ማቅረብ የሚችል



አዱኛ ደበላ ቦቲ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

### 5.2.11 የወጪ ቡና ቆይነት ብቃት ማረጋገጫ

የወጪ ቡና ቆይነት የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1) በአንቀጽ 2.6 ወይም 2.7 ላይ የተጠቀሱትን የቴክኒክ መስፈርቶች የሚያሟላ የቡና መቁያና መፍጫ ኢንዱስትሪ እና የቡና ጣዕም ምርመራ ላብራቶሪ ያለዉ ስለመሆኑ የባለቤት ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል እና የኢንዱስትሪ የብቃት ማረጋገጫ የሚያቀርብ፣
2) ለግል አመልካች ለሥራው የሚያስፈልግ ቢያንስ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ ብር) እና የአንድ ዓመት የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሚያሳይ ከሚመለከተው ባንክ የተረጋገጠ የሰነድ ማስረጃ የሚያቀረብ፣
3) የብቃት ማረጋገጫ ጠያቂው የንግድ ማህበር ከሆነ ለሥራው የሚያስፈልግ ብር 1,000,000 (አንድ ሚሊየን ብር) በባንክ የተረጋገጠ ማስረጃ እና ከመስራቾቹ ቢያንስ ሁለት ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ያላቸው አባላት የአንድ ዓመት የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሚያሳይ ከሚመለከተው ባንክ የተረጋገጠ የሰነድ ማስረጃ እና በሚመለከተው የመንግስት ተቋም የተረጋገጠ የመተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ጽሑፍ የሚያቀርብ፣
4) የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል፣
5) የግብር ከፋይ መለየ ቁጥር ማቅረብ የሚችል፣
6) ከፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ከወንጀል ነጻ ስለመሆኑ የጣት አሻራ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣ የብቃት ማረጋገጫ ጠያቂው የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ ሊቀ መንበር የጣት አሻራ እና የተመረጠበትን የጠቅላላ ጉባኤ ቃሌ ጉባኤ የሚያቀርብ፣
7) የቋሚ ንብረት ማረጋገጫ ሰነድ ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም የሚያቀርብ፣የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን ወይም ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ያለው አባል ቋሚ ንብረት ማስረጃ የሚያቀርብ እና የዋና የሥራ አድራሻ ማረጋገጫ ሰነድ የሚያቀርብ እና
8) የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን ወይም የማህበሩን አስተዳዳሪ ወይም ሊቀመንበር በማንኛውም ንግድ ወይም በማምረት ሥራ ወይም በሙያው ተሰማርቶ መልካም አፈጻፀምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል መሆን አለበት፡፡

### 5.2.12 የሀገር ውስጥ ቡና ቆይነት ብቃት ማረጋገጫ

የሀገር ውስጥ ቡና ቆይነት የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1) በአንቀጽ 2.6 ወይም 2.7 ላይ የተጠቀሱትን የቴክኒክ መስፈርቶች የሚያሟላ የቡና መቁያና መፍጫ ኢንዱስትሪ እና የቡና ጣዕም ምርመራ ላብራቶሪ ያለዉ ስለመሆኑ የባለቤት ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል እና የኢንዱስትሪ የብቃት ማረጋገጫ የሚያቀርብ፣
2) ለግል አመልካች ለሥራው የሚያስፈልግ ቢያንስ ብር 100,000 (መቶ ሺህ ብር) እና የአንድ ዓመት የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሚያሳይ ከሚመለከተው ባንክ የተረጋገጠ የሰነድ ማስረጃ የሚያቀረብ፣



አዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

3) የብቃት ማረጋገጫ ጠያቂው የንግድ ማህበር ከሆነ ለሥራው የሚያስፈልግ ብር 150,000 (መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) በባንክ የተረጋገጠ ማስረጃ እና ከመስራቾቹ ቢያንስ ሁለት ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ያላቸው አባላት የአንድ ዓመት የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሚያሳይ ከሚመለከተው ባንክ የተረጋገጠ የሰነድ ማስረጃ እና በሚመለከተው የመንግስት ተቋም የተረጋገጠ የመተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ጽሑፍ የሚያቀርብ፣

4) የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል፣

5) የግብር ከፋይ መለየ ቁጥር ማቅረብ የሚችል፣

6) ከፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ከወንጀል ነጻ ስለመሆኑ የጣት አሻራ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣ የብቃት ማረጋገጫ ጠያቂው የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ ሊቀ መንበር የጣት አሻራ እና የተመረጠበትን የጠቅላላ ጉባኤ ቃሌ ጉባኤ የሚያቀርብ፣

7) የቋሚ ንብረት ማረጋገጫ ሰነድ ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም የሚያቀርብ፤የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን ወይም ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ያለው አባል ቋሚ ንብረት ማስረጃ የሚያቀርብ እና የዋና የሥራ አድራሻ ማረጋገጫ ሰነድ የሚያቀርብ እና

8) የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን ወይም የማህበሩ አስተዳዳሪ ወይም ሊቀመንበር በማንኛውም ንግድ ወይም በማምረት ሥራ ወይም በሙያው ተሰማርቶ መልካም አፈጻፀምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል ሲሆን ነው፡፡

### 5.2.13 በቡና ንግድ ስራ ውክልና ተቀባይ የብቃት ማረጋገጫ

በቡና ንግድ ስራ ውክልና ተቀባይ የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

ሀ/ የሀገር ውስጥ በቡና ንግድ ስራ ውክልና ተቀባይ የብቃት ማረጋገጫ

1) የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል፣
2) አግባብ ባለው የመንግስት አካል የተረጋገጠ የውክልና ማስረጃ፣
3) የግብር ከፋይ መለየ ቁጥር ማቅረብ የሚችል፣
4) ከፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ከወንጀል ነጻ ስለመሆኑ የጣት አሻራ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣
5) የቋሚ ንብረት ማረጋገጫ ሰነድ ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም የሚያቀርብ እና
6) አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልኩ የተደራጀ አገልግሎት መስጫ ቢሮ ያለው መሆን አለበት፡፡

ለ/ የቡና ገዥ አገር ውክልና ተቀባይ የብቃት ማረጋገጫ

1) የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል፣
2) አግባብ ባለው የመንግስት አካል የተረጋገጠ የውክልና ማስረጃ፣
3) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ማቅረብ የሚችል፣
4) ከፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ከወንጀል ነጻ ስለመሆኑ የጣት አሻራ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣
5) አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልኩ የተደራጀ አገልግሎት መስጫ ቢሮ ያለው መሆን አለበት፡፡



አዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

6) የየትኛው አገር ካምፓኒ ተወካይ እንደሆነ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣
7) የቡና ላኪዎች ብቻ የገበያ ትስስር መፍጠር እና የተሻለ ዋጋና መጠን ግብይት እንዲኖር የሚሰራ፣
8) የወጪ ቡና ውል ወይም ኮንትራት እንዲከበር የሚሰራ፣
9) በወጪ ቡና ግብይት ሥራዎች ለሚገጥሙ ችግሮች መፍታት ባለስልጣኑ በሚያስቀምጠው አቅጣጫ የመፍትሄ አካል ሆኖ የሚሰራ፣
10) የድርጅቱ አመታዊ የግዢ እቅድ በቡና ዓይነትና መጠን አፀድቆ ማቅረብ የሚችል፣
11) በየወሩ የአፈፃፀም ሪፖርት ለባስልጣኑ ሪፖርት ማቅረብ የሚችል፣
12) በብሄራዊ ባንክ በተመዘገበው ከአማካይ ዋጋ በላይ ለመግዛት የግዴታ ውል የሚገባ፣

**5.2.14 የማጓጓዝ አገልግሎት ሰጪነት ብቃት ማረጋገጫ**

የማጓጓዝ አገልግሎት ሰጪነት ብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1) በአንቀጽ 4.8 ላይ የተጠቀሱትን የቴክኒክ መስፈርቶች የሚያሟላ የቡና ጭነት ተሽከርካሪ ያለዉ ስለመሆኑ የባለቤት ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል እና የተሽከርካሪ የብቃት ማረጋገጫ የሚያቀርብ፣
2) የንግድ ማህበር ከሆነ ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም የተረጋገጠ የመተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ጽሑፍ የሚያቀርብ፣
3) የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል፣
4) የግብር ከፋይ መለየ ቁጥር ማቅረብ የሚችል እና
5) ከፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ከወንጀል ነጻ ስለመሆኑ የጣት አሻራ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣ የብቃት ማረጋገጫ ጠያቂው የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ ሊቀ መንበር የጣት አሻራ እና የተመረጠበትን የጠቅላላ ጉባኤ ቃለ ጉባኤ ሊያቀርብ የሚችል መሆን አለበት፡፡

**5.2.15 የቡና ጥራትና ጣዕም ምርመራ ላብራቶሪ አገልግሎት ሰጪነት ብቃት ማረጋገጫ**

የቡና ጥራትና ጣዕም ምርመራ ላብራቶሪ አገልግሎት ሰጪነት ብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1) በአንቀጽ 2.7 ላይ የተጠቀሱትን የቴክኒክ መስፈርቶች የሚያሟላ የቡና ጣዕም ምርመራ ላብራቶሪ ያለዉ ስለመሆኑ የባለቤት ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል፣
2) የንግድ ማህበር ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት ተቋም የተረጋገጠ የመተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ጽሑፍ የሚያቀርብ፣
3) የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል፣
4) የግብር ከፋይ መለየ ቁጥር ማቅረብ የሚችል እና
5) ከፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ከወንጀል ነጻ ስለመሆኑ የጣት አሻራ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣ የብቃት ማረጋገጫ ጠያቂው የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ ሊቀ መንበር የጣት አሻራ እና የተመረጠበትን የጠቅላላ ጉባኤ ቃለ ጉባኤ ማቅረብ አለበት፡፡



ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)

### 5.2.16 የተሸጠ የወጪ ገበያ ቡና ማከማቻ አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ

የተሸጠ የወጪ ገበያ ቡና ማከማቻ አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1) በአንቀጽ 2.4 ላይ የተጠቀሱትን የቴክኒክ መስፈርቶች የሚያሟላ የቡና ማከማቻ መጋዘን ያለዉ ስለመሆኑ የባለቤት ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል ማስረጃ የሚያቀርብ፣
2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2.5 ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶችን ያሟላ፤
3) ለሚያከማቸው ቡና የመድን ዋስትና ማቅረብ የሚችል፣
4) የንግድ ማህበር ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት ተቋም የተረጋገጠ የመተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ጽሑፍ የሚያቀርብ፣
5) የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል፣
6) የግብር ከፋይ መለየ ቁጥር ማቅረብ የሚችል፣
7) ከፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ከወንጀል ነጻ ስለመሆኑ የጣት አሻራ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣ የብቃት ማረጋገጫ ጠያቂው የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ ሊቀ መንበር የጣት አሻራ እና የተመረጠበትን የጠቅላላ ጉባኤ ቃሌ ጉባኤ ማቅረብ የሚችል እና
8) የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን ወይም የማህበሩ አስተዳዳሪ ወይም ሊቀመንበር በማንኛውም ንግድ ወይም በማምረት ሥራ ወይም በሙያው ተሰማርቶ መልካም አፈጻፀምና ስም ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማምጣት የሚችል መሆን አለበት፡፡

### 5.2.17 የልማትና ግብይት ትስስር የብቃት ማረጋገጫ

የልማትና ግብይት ትስስር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት አመልካቹ፡-

1) የአልሚ ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል፣
2) የቡና ልማት ኢንቨስትመንት ፈቃድና የ30 ሄክታርና ከዚያ በላይ የመሬት ሊዝ ውል የሚያቀርብ፣
3) ዘመናዊ የቡና አመራረት ዘዴ ለማስፋፋት ለስራው አግባብ ያለው ባለሙያ ማሰማራቱ እና የእርሻ መሳሪያዎች ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣
4) በትስስሩ የሚታቀፉትን አነስተኛ ቡና አምራች አርሶ አደሮች የመሬት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፣
5) የንግድ ማህበር ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት ተቋም የተረጋገጠ የመተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ጽሑፍ የሚያቀርብ፣
6) የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል፣
7) የግብር ከፋይ መለየ ቁጥር ማቅረብ የሚችል እና
8) ከፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ከወንጀል ነጻ ስለመሆኑ የጣት አሻራ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣ የብቃት ማረጋገጫ ጠያቂው የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ ሊቀ መንበር የጣት አሻራ እና የተመረጠበትን የጠቅላላ ጉባኤ ቃሌ ጉባኤ ማቅረብ አለበት፡፡



አዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

### 5.2.18 የቡና ጫኝና አውራጅነት አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ

የቡና ጫኝና አውራጅነት አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት አመልካቹ፡-

1) በሚመለከተው የመንግስት ተቋም የተረጋገጠ የጫኝና አውራጅ ማህበር የመተዳደሪያ ደንብ የሚያቀርብ፣
2) የማህበሩ ሊቀመንበር የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል፣
3) አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልኩ የተደራጀ አገልግሎት መስጫ ቢሮ ያለው፣
4) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ማቅረብ የሚችል፣
5) የማህበሩ ሊቀ መንበር ከፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ከወንጀል ነጻ ስለመሆኑ የጣት አሻራ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል እና
6) የማህበሩ ሊቀ መንበር መልካም ስነምጋባር ያለው ስለመሆኑ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ማስረጃ የሚያቀርብ መሆን አለበት፡፤

### 5.2.19 የቡና ገለባ አቀነባባሪነት ብቃት ማረጋገጫ

ማንኛውም የቡና ገለባ አቀነባባሪነት ወደ ቡና ገለባ ማቀነባበር ሥራ ከመሠማራቱ በፊት የሚከተሉትን መሥፈርቶች አሟልቶ መገኘት አለበት፡-

1) በአንቀጽ 2.9 ላይ የተጠቀሱትን የቴክኒክ መስፈርቶች የሚያሟላ የቡና ገለባ ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለዉ ስለመሆኑ የባለቤት ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል እና የኢንዱስትሪ የብቃት ማረጋገጫ የሚያቀርብ፣
2) የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል፣
3) የግብር ከፋይ መለየ ቁጥር ማቅረብ የሚችል፣
4) የኢንዱስትሪ የግንባታ ፈቃድ የሚያቀርብ
5) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2.5 ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶችን ያሟላ፤
6) ከፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ከወንጀል ነጻ ስለመሆኑ የጣት አሻራ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣ የብቃት ማረጋገጫ ጠያቂው የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ ሊቀ መንበር የጣት አሻራ እና የተመረጠበትን የጠቅላላ ጉባኤ ቃሌ ጉባኤ
7) ባለስልጣኑ ለአገልግሎት ሰጪዎች ያዘጋጀውን የግዴታ ውል መቀበሉን በፊርማ ያረጋገጠ

### 5.2.20 የቡና ቅጠል ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ብቃት ማረጋገጫ

ማንኛውም የቡና ቅጠል አቀነባባሪ ኢንዱስትሪ ወደ ቡና ቅጠል ማቀነባበር ሥራ ከመሠማራቱ በፊት የሚከተሉትን መሥፈርቶች አሟልቶ መገኘት አለበት፡-

1) በአንቀጽ 2.10 ላይ የተጠቀሱትን የቴክኒክ መስፈርቶች የሚያሟላ የቡና ቅጠል ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ያለዉ ስለመሆኑ የባለቤት ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል እና የኢንዱስትሪ የብቃት ማረጋገጫ የሚያቀርብ፣
2) የማንነት መታወቂያ/ፓስፖርት ማቅረብ የሚችል፣
3) የግብር ከፋይ መለየ ቁጥር ማቅረብ የሚችል፣



ጀዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

4) የኢንዱስትሪ የግንባታ ፈቃድ የሚያቀርብ፣
5) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2.5 ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶችን ያሟላ;
6) ከፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ከወንጀል ነጻ ስለመሆኑ የጣት አሻራ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣ የብቃት ማረጋገጫ ጠያቂው የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ ሊቀ መንበር የጣት አሻራ እና የተመረጠበትን የጠቅላላ ጉባኤ ቃሌ ጉባኤ ማቅረብ የሚችል እና
7) ባለስልጣኑ ለአገልግሎት ሰጪዎች ያዘጋጀውን የግዴታ ውል መቀበሉን በፊርማ ያረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

### 5.3 የብቃት ማረጋገጫ ስለማሳደስ

የብቃት ማረጋገጫ ለማሳደስ አመልካቹ፡-

1) የብቃት ማረጋገጫ እድሳት ቅጽ በመሙላት በደንቡና በዚህ መመሪያ የተገለጹትን መስፈርቶች ስለሚሟላቱ የሚያሳዩ ማስረጃዎችን አያይዞ ማቅረብ አለበት፣
2) የግብር ክሊራንስ ማቅረብ አለበት፣
3) ያለፈውን ዓመት የቡና ምርት ዝግጅት፣ ግዢ፣ ሽያጭና ክምችት ሪፖርት ማቅረብ አለበት
4) የአቅርቦት ቡና ግብይት ወይም ዝግጅት ላይ የተሰማራ ከሆነ የቅድመዝግጅት ስራ ያጠናቀቀ እና ባለፈው ዓመት የገዛውን ምርት ለገበያ ያቀረበ ሲሆን፣
5) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እድሳት ጊዜ በበጀት ዓመቱ፡-
   ሀ/ ለቡና አቅራቢ ከመስከረም 1 ቀን እስከ ሕዳር 30 ቀን ድረስ ነው፣
   ለ/ ለቡና ላኪ ከሕዳር 1 ቀን እስከ የካቲት 30 ቀን ድረስ ነው፤
   ሐ/ ሌሎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ታህሳስ 30 ቀን ድረስ ነው፡፡
6) አሳማኝ ምክንያት መኖሩን በማስረጃ አስደግፎ ካልቀረበ በስተቀር በበጀት ዓመቱ ወደ ሥራ ያልገባ ሰው ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማሳደስ አይችልም፣
7) አሳማኝ ምክንያት መኖሩን በማስረጃ አስደግፎ ካልቀረበ በስተቀር በበጀት ዓመቱ የሽያጭ ውል በውሉ መሠረት የልፈጸመ ሰው ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማሳደስ አይችልም፣
8) ቀድም ብሎ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወስዶ የአደራሻ ላውጥ ያደረገ እና ይህንኑ ያሳወቀ እንደሆነ በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል ታይቶ በተለወጠው አድራሻ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጠዋል፡፡
9) በግብይት ሂደት ህገ ወጥ ድርጊት ውስጥ መሳተፉ የተረጋገጠበት ሰው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አይታደስለትም፡፡

### 5.4 የብቃት ማረጋገጫ ስለማገድ

1) በደንቡ ላይ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን የሚያሳግዱ ጥፋቶች እንደተጠበቀ ሆነው የብቃት ማረጋገጫ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊታገድ ይችላል፡-



ጁዱኖ ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

ሀ/ በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የተጠየቀውን መረጃ ወይም ሰነድ በወቅቱና በአግባቡ ያላቀረበ ከሆነ፣

ለ/ ያስመዘገበውን የንግድ ወይም የሥራ አድራሻ ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል ሳያሳውቅ የቀየረ እንደሆነ፣በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጫ ክፍል የሥራ ኃላፊ የእገዳውን ምክንያት የሆኑትን ጉድለቶች መዝግቦ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤቱ ጉድለቶችን እንዲያስተካክል በጽሁፍ አሳውቆ እስከ 30 ቀናት ብቃት ማረጋገጫውን አግዶ ሊያቆይ ይችላል። እገዳውንም ለሚመለከታቸው አካልም በጽሁፍ ያሳውቃል።

2) በተሰጠው የጊዜ ገደብ ጉድለቶቹን አስተካክሎ በጽሁፍ ለባለስጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል ካሳወቀና ይህም ከተረጋገጠ እገዳው ወዲያው ይነሳል። ለሚመለከተው አካልም በጽሁፍ ያሳውቃል።

## 5.5 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ

1) በደንቡ ላይ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን የሚያሰርዙ ጥፋቶች እንደተጠበቁ ሆነው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሰረዝ ይችላል፦

ሀ/ የቡና ንግድ ሥራውን በራሱ ፍቃድ የተወ እንደሆነ እና

ለ/ የብቃት ማረጋገጫው የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ዓላማ ውጪ ሲጠቀምበት የተገኘ ከሆነ ነው።

2) በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል ስረዛውን የወሰነው ክፍል የስረዛውን ምክንያት ጠቅሶ ለባለጉዳዩና ለሚመለከታቸው አካላት በጽሁፍ ያሳውቃል።

3) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰረዘበት ሰው የሥራ ክፍሉ የሰጠውን ውሳኔ የሚቃወም ከሆነ ቅሬታውን በጽሁፍ ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል የበላይ ኃላፊ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይችላል።

4) የባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል የበላይ ኃላፊ የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።

5) ቅሬታ አቅራቢው ባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የበላይ ኃላፊ በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማማ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል።

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለሥልጣን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Coffee & Tea Development & Marketing Authority



እዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

## ክፍል ስድስት

## ስለአማራጭ ግብይት አሠራር

### 6.1 ቀጥተኛ የግብይት ትስስር አሠራር

#### 6.1.1 ቀጥተኛ የግብይት ትስስር ስለመፍቀድ

1) ቀጥተኛ የግብይት ትስስር የሚፈቀደው የወጪ ገበያ ቡና ንግድ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና የንግድ ፈቃድ በተሰጠው ቡና ላኪ ወይም የወጪ ገበያ ቡና ቆዪ እና የአቅራቢነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከተሰጠው ቡና አቅራቢ ወይም አልሚ ባለሃብት ጋር ትስስር ሲፈጠር ነው፡፡
2) ትስስሩ የተፈጠረበት ውል በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ አካል መረጋገጥ አለበት፡፡
3) የቀጥተኛ የግብይት ትስስር ዕውቅና የሚጠይቅ ሰው ባለስልጣኑ ጋር በመቅረብ የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡
4) የቀጥተኛ የግብይት ትስስር ተዋዋይ ቡና አቅራቢ በየዓመቱ ለትስስሩ ከሚያዘጋጀው ሰባአምስት በመቶ ቡና ሙሉ ለሙሉ ለተዋዋይ ቡና ላኪው ብቻ ማስረከብ አለበት፡፡
5) የቀጥተኛ የግብይት ትስስር ተዋዋይ ቡና ላኪ በየዓመቱ በደንቡ መሠረት በቡና አቅራቢው ለትስስሩ የተዘጋጀን ቡና ሙሉ ለሙሉ ክፍሎ መረከብ አለበት፡፤
6) የተረጋገጠ ውል ለሚያቀርቡ አመልካቾች ባለስልጣኑ በደንቡ የተጠቀሱት አስገዳጅ የውል ቃሎች በውሉ መካተታቸውን አረጋግጦ የዕውቅና ሰርቲፊኬት ይሰጣል፡፡
7) የቀጥተኛ ግብይት ትስስር ሥራ ዕውቅና የተሰጠው አካል ቡናው ከአቅራቢ የተረከበው ቡና በዕለቱ ከነበረው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ አማካይ ዋጋ በታችና እኩል መመዝገቡ ሲረጋገጥ እንዲሁም የወጪ ቡና ሽያጭ ውሉ በዕለቱ ከነበረው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አመካይ ዋጋ በታች መሆኑ ሲረጋገጥ ባለስልጣኑ የሰጠውን እውቅናውን ያነሳል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፡፡

#### 6.1.2 ቀጥተኛ የግብይት ትስስር አፈጻፀም

1) በቀጥተኛ የግብይት ትስስር የታቀፈ አቅራቢ ያዘጋጀውን ቡና ወደ ቡና ጥራት ምርመራ ደረጃ ምደባ ማዕከል በማቅረብ በውሉ መሠረት በቡና ዓይነትና መጠን ደረጃ ያስወጣል፣ ደረጃ የወጣለትን ቡና ዋጋ በዕለቱ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ዋጋ መሠረት በማዕከሉ ያስመዘግባል፣
2) በዚህ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በቀረበው የቡና ዓይነትና ጥራት ደረጃ መሠረት በዕለቱ የተመዘገበው አማካይ የቡና ዋጋ የልተፈጸመ ከሆነ ካለፉት የግብይት ቀናት የመጨረሻው የዕለቱ አማካይ ዋጋ በላይ ሆኖ ሊመዘገብ ይችላል፡፡
3) የምርመራ ውጤቱ በትስስሩ ውል መሠረት ቡናው በውሉ ከተስማሙት ውጪ ከሆነ ቡናው በምርት ገበያው ይሸጣል፡፡ ሆኖም በምርመራው ሂደት ላይ ቅሬታ ከቀረበ ምርመራው በድጋሚ እንዲታይ ወይም/እና በሶስተኛ ወገን ዳኝነት እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡
4) ላኪው በቀጥተኛ የግብይት ትስስር መሠረት የተረከበውን ቡና ወደ ወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ እንዲሸኝለት ለባለስልጣኑ የሸኝት ሠራተኛ ጥያቄ ያቀርባል፡፡



እዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

5) የባለስልጣኑ ቡና ሸኚ በቀጥተኛ የግብይት ትስስር መሠረት በመመዝግብ ወደ ላኪ. ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ በፕሎምፕ አሽጎ ይሸኛል፡፡
6) ላኪ.ው በውሉ መሠረት ቡና በዓይነት በመጠን በዋጋ የምርት መረከቢያ ደረሰኝ ለአቅራቢ. ይሰጣል ወዲያውኑ ኮፒውንም ለባለስልጣኑ በኤሌክትሮኒክስ ወይም በሀርድ ኮፒ ይሰጣል፡፡
7) በቀጥተኛ  የግብይት ትስስር ዕውቅና ያገኘ ላኪ. በተራ ቁጥር 6.1.1 ተጠቀሰው መሠረት ተመዝግቦ የተረከበውን ቡና በመጠን፣ ዓይነት፣ ደረጃ እና ዋጋ መረጃ ለባለስልጣኑ በየወሩ ማሳወቅ አለበት፣
8) ላኪ. በትስሰር ያገኘውን ቡና ገበያ አፈላልጎ በተሻለ ዋጋ መሸጥ ያለመቻሉ ከተረጋገጠ ባለስልጣኑ ትስስሩ እንዲቋረጥ ያደርጋል፡፡

## 6.2 የልማትና ግብይት ትስስር አሠራርና አፈጻጸም

1) የአልሚ ላኪ.ነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በባለስልጣኑ የተሰጠው አልሚ ላኪ. የልማትና ግብይት ትስስር ውል ከአርሶአደሮች ጋር በመፈጸም በሰነዶች ምዝገባና ማረጋጫ አካል የተረጋገጠ ውል አግባብ ላለው የክልል አካል ያቀርባል፡፡
2) አግባብ ያለው የክልል አካል በደንቡ እና በዚህ መመሪያ የተገለጹትን መሠረታዊ የውል ቃሎች መሟላታቸውን አረጋግጦ ለአልሚ ላኪ.ው የልማትና ግብይት ትስስር ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
3) ስለቡና ግዥ፣ ክምችት፣ ዝግጅት፣ እሴት ጭመራና ሽያጭ መረጃ ለባለስልጠኑ እና አግባብ ባለው የክልል አካል በየወሩ ማቅረብ አለበት፣
4) አግባብ ያለው የክልል አካል የልማትና ግብይት ትስስር ውል አፈጻጸም  ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

## 6.3 የኮንትራት ቡና ልማት አሰራር እና አፈፃፀም

የኮንትራት ቡና ልማት አሰራር ከአነስተኛ ይዞታ ባላቸው ቡና አምራች አርሶ አደሮች እና በወጪ. ቡና ቆይ ኢንዱስትሪዎች ጋር ስምምነት ከተደረገ በኃላ የወጪ. ቡና ቆዩ ኢንዱስትሪው በባለስልጣኑ ቀርቦ የትስስር ዕውቅና የምስክር ወረቀት ለማግኙት የሚከተለውን መሟላት አለበት፡፡

1) የወጪ. ቡና ቆዩነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና የንግድ  ፍቃድ ሲ.ኖር፤
2) አግባብ ባለው የክልል አካል የተረጋገጠ በትስስሩ ከሚ.ታቀፉ ቡና አምራች አርሶ አደሮች ስም፣ ብዛት፣ በቡና የተሸፈነ ማሳ እና የቡና እግር ብዛት፣ የምርት ግምት መጠን የሚ.ያሳይ ማስረጃ እና ከአርሶአደሮቹ ጋር የተደረገ የመብትና ግዴታ  የቃለ-ጉባኤ ሰነድ ማቅረብ የሚ.ችል፣
3) እሽት ቡና ወይም ጀንፈል ቡና ለማዘጋጀት የራሱ ወይም በኪ.ራይ ውል የተገኘ ማዘጋጃና ማከማቻ ያለው ስለመሆኑ አግባብ ካለው የክልል አካል ማስረጃ የሚ.ያቀርብ፣
4) ለምርታማነት እድገትና ጥራት መሻሻል አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች በውል ስምምነት መሠረት በትስስሩ ለታቀፉ ቡና አምራች አርሶአደሮች ለማቅረብ የሚ.ስማማ ሲ.ሆን፤
5) በትስስሩ ለታቀፉ ቡና አምራች አርሶ አደሮች እሸት ቡና ወይም ጀንፍል ቡና ሲ.ረከብ ከአከባባ ገበያ ዋጋ በላይ ለመክፈል የሚ.ስማማ፣



እዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

6) በየምርት ዘመኑ በትስስሩ ስር ያሉ አርሶአደሮች የለማ ማሳ መጠን፣ ምርት የሚሰጥ ማሳ፣ ጥቅም ላይ የዋለ የግብዓት ዓይነትና መጠን፣ ምርትና ምርታማነት በኪ.ሎ ግራምና የግዥ ዋጋ መረጃ አደራጅቶ ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል ለማቅረብ የተስማማ፤ሲሆን ነው፡፡

7) የኮንትራት ግብይት ትስስር ዕውቅና ሰርተፊኬት በባለስልጣኑ የተሰጠው የወጪ ቡና ቆዩ ኢንዳስትሪ የኮንትራት ግብይት ትስስር ውል ከአርሶአደሮች ጋር በመፈጸም ውሉን በሰነዶች ምዝገባና ማረጋጫ አካል አረጋግጦ አግባብ ላለው የክልል አካል የቀርባል፡

8) አግባብ ያለው የክልል አካል የቀረበለትን የኮንትራት ግብይት ትስስር ውል በደንቡ እና በዚህ መመሪያ የተገለጹትን መሠረታዊ የውል ቃሎች መሟላታቸውን አረጋግጦ ውሉን ያጸድቃል፡፡

9) ስለቡና ግዥ፣ ክምችት፣ ዝግጅት፣ እሴት ጭመራና ሽያጭ መረጃ ለባለስልጠኑ እና አግባብ ባለው የክልል አካል በየወሩ ማቅረብ አለበት፣

10) አግባብ ያለው የክልል አካል የኮንትራት ቡና ልማት ትስስር ውል አፈጻጸም ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

### 6.4 በቡና ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከላት የአማራጭ የቡና ግብይት አመዘጋገብ

1) ማንኛውም በአማራጭ የቡና ግብይት አሠራር የተፈጸመ የቡና ግብይት ወደ ቡና ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል ቀርቦ ዓይነት፣ ደረጃ፣ መጠንና የዕለቱ የምርት ገበያ ዋጋ መመዝገብ አለበት፡፡

2) የቀረበው ቡና መጠን ሲመዘገብ ቡናውን የጫነው ተሽከርካሪ ነጠላ ክብደቱ አስቀድሞ የተመዘነ መሆኑን የሚገልጽ የክብደት ልኬት በዘመኑ በተመረመረ የምድር ሚዛን የተመዘነበትን ውጤት ቀርቦ ይመዘገባል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ስለቡና ሽኝት አፈጻጸም

### 7.1 የቡና ሽኝት የሚካሄድባቸው ስፍራዎች

የቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና፣ የአቅርቦት ወይም ኤክስፖርት ጥሬ ቡና ወይም የተቆላ ወይም ተቆልቶ የተፈጨ ቡና ወይም የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ሽኝት በሚከተሉት ቦታዎች ብቻ ይፈጸማል፡፡

1) የቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና ከመጀመሪያ ደረጃ ቡና ግብይት ማዕከላት ወደ አቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች፣

2) ከራሳቸው ማሳ ያመረቱት ወይም በልማትና ግብይት ትስስር ወይም በኮንትራት ልማት ትስስር፣ ወይም የልዩ ቡና ዝግጅት አሠራር መሰረት ግብይት የተፈጸመበትን የጀንፈልና እሸት ቡና ወደ አቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ፣

3) በቡና አቅራቢ ወይም አልሚ ባለሃብት ወይም መሠረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት ወይም ዩኒየኖች ወይም አነስተኛ አርሶአደሮች የተዘጋጀ የአቅርቦት ቡና ከወረዳ አቅርቦት ቡና መዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ለሽያጭ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ፣



ዶ/ር ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

4) ከራሳቸው ማሳ ያመረቱት ወይም በአመራጭ የግብይት አሠራር ግብይት የተፈጸመበት ቡና ወይም በህብረት ስራ ማህበራት የተዘጋጀ የአቅርቦት ከወረዳ ለቡና ለጥራት ደረጃ ምርመራ ወደ የቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል፣

5) ከቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል የጥራት ደረጃ የወጣለትን ወይም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ግብይት የተፈጸመበትን የወጪ ገበያ ደረጃ የአቅርቦት ቡና ወደ ኤክስፖርት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች

6) በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ግብይት የተፈጸመበት የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ከምርት ገበያ መጋዘን ወደ ተጠቃሚ አከባቢዎች፣

7) ከኤክስፖርት ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ወደ ሌላ ኤክስፖርት ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ፣

8) ከወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ለወጪ ቡና ዝግጅት የሚወጣ ተረፈ ምርት ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ፤

9) ለወጪ ገበያ የተዘጋጀ ቡና ከማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች በሚሰጠው የዝግጅት ሰርተፊኬት ወደ የምርት ጥራት ምርመራና ሰርተፊከሽን ማዕከል፣

10) ለኤክስፖርት የተዘጋጀ ቡና በምርት ጥራት ምርመራና ሰረተፊከሽን ማዕከል ደረጃው ከተረጋገጠ በኋላ በባለስልጣኑ የሽኝት ሰራተኞች ወደ ወደብ ወይም ወደ ኤርፖርት ወይም ኤክስፖርት ቡና በውጭ ምንዛሪ እንዲሸጡ ወደተፈቀደላቸው መደብሮች፣

11) የቡና ቅጠል ከቡና አምራች ወረዳ ወደ ቅጠል ማቀነባበሪያና ማከማቻ ኢንዱስትሪ እና ወደ ተጠቃሚ አከባቢዎችና ሀገራት፤

12) የቡና ገለባ ማዘጋጃና ማከማቻ ወደ የቡና ጥራት ምርመራና ሰርተፍኬሽን አልፎ ወደ ተጠቃሚ አከባቢዎችና ሀገራት፤

13) ከላይ የተጠቀሱት እንደተጠበቀ ሆኖ በማኛኛውም መልኩ ተሸከርካሪው የመገልበጥ ወይም የቴክኒክ ብልሽት ካጋጠመው በቦታው፣በህጋዊ ይሸኛል።

## 7.2 የሽኝት ሰራተኛ ስለመመደብ

1) የቀይ እሸት ቡና እና ጀንፈል ቡና ግብይት በሚካሄድባቸው የመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት በክልል አግባብ ባለው አካል የሽኝት ሠራተኛ ይመድባል።

2) የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች ባሉባቸው አከባቢዎች አግባብ ባለው የክልል አካል የሽኝት ሠራተኛ ይመድባል።

3) በባለስልጣኑ የቡና ምርት ሽኝት ጣቢያዎች እና በምርት ጥራት ምርመራና ሰርተፊከሽን ማዕከላት በባለስልጣኑ የሽኝት ሠራተኛ ይመድባል።

## 7.3 የቡና ሽኝት አሰራር

### 7.3.1 ቅደመ ሽኝት አሠራር

ማንኛውም የሽኝት ሰራተኛ ቡና ወይም ቡና ቅጠል ወይም ገለባ ከመሸኘቱ በፊት የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማረጋገጥ ይኖርበታል፤



እዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

1) ለግብይት የሚቀርብ የቡና ቅጠል ተፈጥሯዊ አገልግሎቱን አጠናቆ የተሰበሰበ መሆኑን

2) በቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ በመገኘት ስለዝግጅቱ ሁኔታ፣

3) ለግብይት የሚውል የቡና ገለባ በውስጡ ያለው የቡና ፍሬ መጠን ከአንድ ከመቶ በላይ ያልሆነ መሆኑ፣

4) የቡና ቅጠልና ገለባ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ በመገኘት ስለዝግጅቱ ሁኔታ

5) በኢ/ም/ገበያ የተገዛ ወይም በትስስር ወይም ከማህበራት ወደ ዩኒየን ከሆነ ከምርት ገበያ ቅርንጫፎች የተሰጠ የምርት መረከቢያ ሰነድ/GRN/መታየት ይኖርበታል

6) የአልሚ ላኪ ወይም የአቅራቢ ላኪ ከሆነ በምርት ገበያ ቅርንጫፎች የቡና ሚዛን መግለጫ እና ከወረዳ የተሸኘበት ሰነድ መታየት ይኖርበታል

7) ቡናውን ለማጓጓዝ የቀረበው ተሽከርካሪ ቡና የመጫን የብቃት ማረጋገጫ ያለው መሆኑን፣

8) ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሆን የንግድ ፈቃድ፣ የብቃት ማረጋገጫ እና የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ውል መቀበል ያስፈልጋል

9) ቡናው የብቃት ማረጋገጫ ባለው ሰው የተገዛ ወይም የተዘጋጀ መሆኑን፣

10) ቡናውን ለመጫን የተዘጋጀው ተሽከርካሪ የቡና ጥራት ሊያበላሹ ከሚችሉ ባእድ ነገሮች የጸዳ መሆኑን፣ምርቱን ለመሸፈን የሚያስችል ያልተቀደደና ንጹህ የካኪ ሸራ፣ መወጠሪያና ማሰሪያ ገመድ፣

11) ቀድሞ የተሸኘ ማንኛውም ቡና ወደ ተሸኘበት ህጋዊ ቦታ ስለመድረሱ ማረጋገጫ ሰነድ ማቅረቡን፣

### 7.3.2 የቀይ እሸት፣ የጀንፈል ቡና እና የቡና ቅጠል የሸኝት አሰራር

1) በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ግብይት የተፈጸመበት የቀይ እሸትና ጀንፈል ቡና ጥራቱ ተፈትሾ ወደ አቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች በይለፍ ወረቀት ይሸኛል።

2) ማንኛውም ለግብይት የሚቀርብ የቡና ቅጠል ወደ ቡና ቅጠል ማቀነባበሪያ በይለፍ ወረቀት ይሸኛል፤

3) የሸኝት አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያ የቡናውን መጠን፣ ዓይነት፣ የቡናውን ባለቤት፣ ቡናው የሚሸኝበትን ኢንዱስትሪ፣ የተሽከርካሪ አይነትና የሰሌዳ ቁጥር፣ ቡናው የሚጓጓዝበትን መስመር፣ መነሻ ሰዓት፣ ቡናው የሚጓጓዝበትን ኢንዱስትሪ ርቀት ከግምት በማስገባት መድረስ ያለበትን ሰዓት የሚገልጽ የተፈረመ የይለፍ ወረቀት ለአጓጓዡ ይሰጣል።

4) የቡናው ወይም የቡና ቅጠል ባለቤት ወይም ሕጋዊ ውክልና የያዘ ወኪል ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና ወይም የቡና ቅጠል ሲያጓጉዝ በዚህ ንዑስ አንቀጽ1 እና 2 መሰረት የተሰጠ የይለፍ ወረቀት የመያዝ ግዴታ አለበት፣

5) አቅራቢው ሌላ የሸኝት ጥያቄ ሲያቀርብ ቀደሞ የተሸኘውን ቡና ማድረሱን ከተሸኘበት ኢንዱስትሪ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፣



እዱኛ ደበላ ቦቱ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

### 7.3.3 የአቅርቦት ቡና የሽኝት አሰራር

ከአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች ቡና ሲሸኝ የሚከተለውን የአሰራር ስርዓት መከተል አለበት፤

1) በአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ የተዘጋጀ የአቅርቦት ቡና የታሸገበትን ጆንያ፣ የተሸከርካሪውን የሸራ ደህንነትና ጽዳት እንዲሁም የቡናው ጠቅላላ መጠን ተረጋግጦ፣ በፕሎምፕ ታሽጎና ተጨፍልቆ የመሸኛ ሰነድ ተሰጥቶት ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ይሸኛል።
2) በአማራጭ የቡና ግብይት አሠራር የተዘጋጀ የአቅርቦት ቡና የታሸገበትን ጆንያ፣ የተሽከርካሪውን የካኪ. ሸራ ደህንነትና ጽዳት እንዲሁም የቡናው ጠቅላላ መጠን ተረጋግጦ፣ በፕሎምፕ ታሽጎና ተጨፍልቆ የመሸኛ ሰነድ ተሰጥቶት ለጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ወደ ቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል ይሸኛል፤
3) ማንኛውም የአቅርቦት ቡና የጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ የተሰጠው ቡና ወደ የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ይሸኛል፤
4) የሽኝት አገልግሎት ሲሰጥ የቡናው መጠን በኪሎ ግራም፣ አይነት፣ ባለቤት፣ የተመረተበት ኢንዱስትሪ እና አከባቢ፣ የሚጓጓዝበት መስመር፣ መነሻ ቀንና ሰዓት፣ መድረሻ ቦታ እና ሌሎች በመሸኛ ቅጹ የተዘረዘሩ መረጃዎች በህጋዊ የሽኝት ሰነድ ላይ ተገልጾ በሽኝት ባለሙያ ተፈርሞ እና የሚመለከተው የመንግስት ተቋም ማህተም ተደርጎበት ይሸኛል፣
5) በቡና አምራች አካባቢዎች የቡና ሽኝት አገልግሎት ሲሰጥ የቡናውን የጥራት ሁኔታ ለመመርመር የሚወሰድ ናሙና ወዲያው ለባለቤቱ ይመለስለታል፣
6) የአቅርቦት ቡናው ባለቤት ወይም ህጋዊ ወኪል ወይም አጓጓዥ ቡና ሲያጓጉዝ መሸኛ ሰነድ የመያዝ ግዴታ አለበት።
7) አቅራቢው ወይም ላኪ ወይም ህብረት ስራ ማህበር ወይም አልሚ ባለሃብት ወይም አነስተኛ ይዞታ ያለው አርሶ አደር መጀመሪያ በተሰጠው የሽኝት ሰነድ መሰረት ቡናውን ወደተሸኘበት ቦታ ስለማድረሱ ማረጋገጫ የማቅረብ ግዴታ ይሆናል።
8) የሽኝት ባለሙያ የተከናወኑ የሽኝት ተግባራት በሚመለከት ወቅታዊ የሽኝት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል ያቀርባል።

### 7.3.4 የወጪ ገበያ ቡና የሽኝት አሠራር

የወጪ ገበያ ቡና ሲሸኝ የሚከተሉት አሠራሮችን መከተል ይኖርበታል፣

1) በቡና ጥራት ምርመራና ሰርተፊከሽን ማዕከል በሚሰጠው የምርመራ መስፈርት መሠረት ሰርቲፊኬት ማግኘት አለበት።
2) የወጪ ገበያ ቡና ለመጫን ፈቃድ በተሰጠው ተሽከርካሪ ወይም ባቡር ላይ በኮንቴነር መጫን አለበት፣
3) የወጪ ቡና ገበያ ሲሸኝ ቡና እንዲጫን የባንክ የጭነት ፈቃድ፣ የትራንዚት ሰነዶች፣ ከጉሙሩክ ኮሚሽን የሽኝት ሰነዶች ማሟላት አለበት።



እዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

4) ቡናዉ በአውሮፕላን የሚጫን ከሆነ በአውሮፕላን ለመጫን ፈቃድ የተሰጠው ኮንቴይነር ወይም ማሸጊያ ካርቶን ወይም ጆንያ የተሞላ ቡና ሆኖ ሲገኝ ወይም ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ወይም በሌሎች አየር መንገድ የካርጎ ወይም የጭነት ጉዞ ትኬት ያለው መሆን አለበት፡፡

5) የሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች የማዘጋጀትና የማከማቸት ውል ሲቋረጥ ውሉ ከተቋረጥበት ኤክስፖርት ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ወደ አዲስ ውል ወደ ተፈጸመበት ኤክስፖርት ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ይሸኛል፡፡

6) ከላይ ከተራ ቁጥር 1-5 የተጠቀሱት ሁኔታዎች መሟላታቸው ሲረጋገጥ የዓለም የቡና ድርጅት መለያ ቁጥር፣ የምስክር ወረቀት ቁጥር፣ የቡናው ዓይነት፣ የጥራት ደረጃ፣ የቡና ምርት ዘመን፣ የሚሄድበት አገር ስም መጻፉን በማየት በፕሎምፕ በማሸግ፣ በመሸኛ ሰነዱ ላይ በመፈረምና የባለስልጣኑን ማህተም በማሳረፍ ይሸኛል፡፡

7) ለውጪ ገበያ የተዘጋጀ እሴት የተጨመረበት ቡና በሀገር ውስጥ በውጭ ምንዛሪ ወደ ሚሸጥበት መደብር ሲሸኝ ከበባለስልጣኑ የተሰጠ ፈቃድ መቅረብ አለበት፡፡

8) የመሸኛ ሰነድ የተሰጠው  ማንኛውም ተሸከርካሪ የሽኝት ስነስርዓት ከፈጸመ በኃላ ወደ ወደብ ጉዞ መጀመሩን የሽኝት ባለሙያው ያረጋግጣል፡፡

9) የባለስልጣኑ የሽኝት ባለሙያ ወደ ወደብ ወይም አየር መንገድ ወይም በሀገር ውስጥ የወጪ ገበያ ቡና በውጭ ምንዛሪ መሽጫ መደብር መሸኘቱን በየዕለቱ ለባለስልጣኑ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

### 7.3.5 የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና የሽኝት አሰራር

1) የቡና ጅምላ ነጋዴው በምርት ገበያዉ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውል የተረጋገጠ ቡና የታሸገበት ጆንያ፣ ጭነቱ የተሸፈነበት ሸራ ታይቶና ተፈትሾ በፕሎምፕ ታሽጎና ተጨፍልቆ ቡና አምራች ወዳልሆኑ ተጠቃሚ አከባቢዎች ይሸኛል፤በተመሳሳይ መልኩ  በቡና አምራች አካባቢ የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ጅምላ ነጋዴዎች በአከባቢዉ ከሚገኝ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ የፍጆታ ቡና በመግዛት ለአከባቢዉ ተጠቃሚ ያቀርባሉ፤ከማንኛዉም የምርት ገበያ ቅርንጫፍ ወደ ቡና አምራች አከባቢ የሚደረግ የሀገር ዉስጥ ፍጆታ ቡና ሽኝት በአከባቢዉ የአቅርቦት እጥረት ስለመኖሩ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለባለስልጣኑ ሲያረጋግጥ ብቻ በልዩ ፍቃድ ይስተናገዳል ፡፡

2) የሽኝት ባለሙያው የሽኝት ጥያቄ ከማስተናገዱ በፊት በጅምላ ነጋዴው ስም ቀድሞ የተሸኘ ቡና ካለ በትክክል መድረሱን የሚያረጋግጥ ሰነድ ተረክቦ ይሸኛል፡፡

3) የሽኝት ባለሙያው የቡናውን መጠን፣ ዓይነት፣ የቡናውን ባለቤት፣ ቡናው የሚሸኝበትን ክልል/ከተማ፣ ቡናው የሚጓጓዝበትን መስመር፣ መነሻ ቀንና ሰዓት፣ የሚገልጽ ሰነድ ለቡናው ባለቤት ወይም ህጋዊ ወኪል ወይም ለአጓጓዥ መስጠት ይኖርበታል፡፡



አዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

## ክፍል ስምንት

## ስለኬላዎች አደረጃጀትና አሠራር ሥርዓት

### 8.1 የሀገ-ወጥ ቡና መቆጣጠሪያ ኬላዎች አደረጃጀት

የቡና ሕገ-ወጥ ዝውውርን ለመከላከል ብቸኛ መዘዋወሪያ መንገድ ወይም በአቅራቢያው ሌላ መሿለኪያ መንገድ በሌለው ቦታ በጥናት ላይ ተመሥርቶ የመቆጣጠሪያ ኬላዎች የሚቋቋሙና የሚደራጁ ሆኖ፦

1) ኬላዎች የሚቋቋሙት በባለስልጣኑ እና በክልል አግባብ ባለው አካል በጋራ ጥናትና ውሳኔ ይሆናል
2) በሌሎች ተቋማት በህግ የተሰጣቸውን የቁጥጥር ተግባር ለመፈጸም የሚቋቋሙ ኬላዎች የቡና ዝውውር እንዲከታተሉ ባለስልጣኑ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡
3) በባለስልጣኑ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር ኬላዎች በክልል አግባብ ባለው አካል ባለቤትነት መመራት ይኖርባቸዋል፡፡
4) መጠለያ፣ ቢሮ፣ ምርት ማቆያ እና ለኬላው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን አግባብ ያለው የክልል አካል ያሟላል፡፡
5) መረጃ በቀላሉ የሚያገኙበትና ግብረ መልስ የሚሰጡበት ስልክ እና እንደአስፈላጊነቱ ኢንተርኔትና ፋክስ እንደሟላ ይደረጋል፡፡
6) በተሟላ መንገድ ለመምራትና ለማስተዳደር በቂ የመንግሥት በጀት ሊመደብ ይገባል፡፡
7) አስፈላጊ በሆነበት ወቅት ማንኛውም ኬላ የተቋቋመለትን ዓላማ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የማያሟላ መሆኑ በጥናት ሲረጋገጥ ሊነሳ ይችላል፡፡
8) በመቆጣጠሪያ ኬላ የሚመደቡ ተቆጣጣሪዎች በመልካም ስነምግባርቸው የተመሠከረላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
9) የሥራው ባህሪ ቀንና ሌሊትን ጨምሮ በዝናብም ሆነ በፀሐይ ሙቀት ወቅት የሚሠራ በመሆኑ ለኬላ ተቆጣጣሪነት የሚመደብ ተቆጣጣሪ ሙሉ አካል ያለውና ጤናማ መሆን ይኖርበታል፡፡

### 8.2 የሀገ-ወጥ ቡና መቆጣጠሪያ ኬላዎች አሠራር

1) የኬላ ተቆጣጣሪው ማንኛውምን ተሽከርካሪ የመፈተሽና የሚጠየቁ ህጋዊ ሰነዶችን የማየት ግዴታ አለበት፡፡
2) ኬላውን በኃይል ጥሶ የሚሄድ ተሽከርካሪ እንዲያዝ ተቆጣጣሪው ቀጥሎ ላለው ቀበሌ/ወረዳ/ከተማ መረጃውን በፍጥነት በማስተላለፍ እንዲያዝ ያደርጋል፡፡
3) በሚመለከተው አካል የሚሰጠው መሸኛ ወረቀት፣ የጭነቱ እሸግ ትክክኛነቱን በማረጋገጥ እንዲሁም የተመሳሰለ /ፎርጅድ/ይሆናል ተብሎ የተጠረጠረውን የሽኝት ሰነድ ወይም ጭነት ከመነሻው እንዲረጋገጥ በማድረግና ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ ያልፋል፡፡
4) ጀንፈል ወይም የቀይ እሸት ቡና ወደ አቅርቦት ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች ሲንቀሳቀስ ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የተሰጠ የቡና መሸኛ ወይም የይለፍ ወረቀት መያዙ ተረጋግጦ ያልፋል፡፡



እዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

5) ከአርሶ አደሮች ወይም ህብረት ሥራ ማህበራት ወይም ከአልሚ ባለሃቶች ወይም አቅራቢዎች ከአቅርቦት ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች ወደ ምርት ገበያ ለሽያጭ ወይም ወደ ኤክስፖርት ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዲስትሪ ሲንቀሳቀስ በወረዳ ቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት ሠራተኛ ወይም የቡና ሽኝት ባለሙያ በኘሎምኘ ታሽጎና ተጨፍልቆ ሕጋዊ የቡና መሸኛ ይዞ የሚንቀሳቀስ ቡና ተፈትሾ ያልፋል፡፡

6) ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የተገዛው ቡና ከኤክስፖርት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች ወይም ወደ ሸማች አከባቢዎቸ ሲጓጓዝ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ዕቃ መረከቢያ እና የባለስልጣኑ የሸኙት ደረሰኝ ወይም በሌሎች አመራጭ የግብይት አሠራሮች መሠረት በባለሥልጣኑ ሸኙት ጣቢያ የሚሰጠው የሸኙት ሰነድ እንዲሁም የጭነቱ አስተሻሸግ ትክክለኛነት በማረጋገጥ ተፈትሾ ያልፋል፡፡

7) በኬላ ፍተሻ ወቅት ከመነሻው የተሸኘበት የሸኙት ሰነዶች ትክክል ሆነው በልዩ ልዩ ምክንያት ሽራው የተቀደደ ከሆነ ወይም መንገድ ላይ መቀደዱን አሽከርከሪው ከሚመለከተው ሕጋዊ አካል መረጃ የሚያቀርብ ከሆነ ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል በማሳወቅ ሕጋዊ መሆኑ ሲረጋገጥ ተስተካክሎ ያልፋል፡፡

8) ማንኛውም ሕጋዊ ቡና የጫነ ተሽከርካሪ ህጋዊ ሰነድ ኖሮት ከተሸኘው ቡና ውጪ ተጨማሪ ቡና ወይም ሌላ ምርት በማንኛውም የተሽከርካሪ አካል ላይ ደርቦ ጭኖ ከተገኘ ተጨማሪውን ቡና ወይም ሌላ ምርት ህጋዊ ደረሰኝ በመስጠት ተይዞ በሕጋዊነት ታሽጎ የተሸኘው ቡና ብቻ ተፈትሾ ያልፋል፡፡

9) ሕጋዊ የሸኙት ሥርዓት ፈጽሞ የሚያልፍ ቡና የጫነ ተሽከርካሪ የተፈተሸበት ቀን፣ ሰዓት፣ የሾፌር ስም፣ መጠን፣ የተሽከርካሪ ሰሌዳ በሰነድ/በመረጃነት መያዝ በሰነዶቹም ላይ ፈታሹ ፊርማውን ሙሉ ስሙን እና ቀኑን ማስቀመጥ አለበት፡፡

10) በሕገ-ወጥነት ሲጓጓዝ የተያዘው ቡና ሙሉ መኪና ወይም በከፊል የተጫነ ከሆነ ታጅቦ በአቅራቢያው ወደ ሚገኝ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ እንዲገባ ይደረጋል፡፡

11) በሕገ-ወጥነት ተጠርጥሮ የተያዘ ቡና መጠኑ አነስተኛ ማለትም ቁርጥራጭ ከሆነ ደረሰኝ ተቆርጦለት በተዘጋጀው ጊዜያዊ ምርት ማቆያ እንዲከማች አድርጎ በአቅራቢያ ለሚገኘው ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው የክልል አካል ያስረክባል፡፡

12) በተሽከርካሪዎች ላይ የሚደረግ ፍተሻ ለአንድ ተሽከርካሪ ቢበዛ ከ45 ደቂቃ በላይ የረዘመ መሆን የለበትም፡፡

13) ቡና ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ለዘር፣ ለናሙና ምርመራ ወይም ለማስተዋወቅ በመሸኛ ሰነድ የተፈቀደ መሆኑን የሚያቀርብ ከሆነ ተመዝግቦ እንዲያልፍ ይደረጋል፡፡

14) ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በሀገር ውስጥ በተለያዩ መጓጓዣዎች ሲዘዋወር ለግል ፍጆታ ደረጃው ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሆነ ቡና እስከ 2 ኪሎግራም ይዞ ማለፍ ይችላል፡፡

15) ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ወደ ውጭ ሀገር ሲጓዝ ለግል ፍጆታ እስከ 2 ኪሎግራም ይዞ ማለፍ ይችላል፡፡



ላ ቦቴ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

16) በኬላ ተቆጣጣሪነት ተመድቦ የሚሠራ ተቆጣጣሪ ለሚያከናውነው ተግባር ተጠያቂ ይሆናል፡፡

17) በአንዱ ኬላ ተፈትሾ ያለፈ ተሽከርካሪ በሌላ ኬላ ሕገ-ወጥ ቡና ከመነሻው መጫኑ ተፈትሾ ከተረጋገጠ የመጀመሪያው ኬላ ላይ ተመድቦ በስራ ላይ የነበረ የኬላ ተቆጣጣሪ ሆን ብሎ ሕገ-ወጥ ተሽከርካሪ እንዳሳለፈ ተቆጥሮ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

18) ሕገ-ወጥ ቡና የጫነውን ተሽከርካሪ ሆን ብሎ ለመጥቀምና አይቶ እንደላየ እንዲያልፍ ያደረገ ወይም ለማሳለፍ የተደራደረ የኬላ ተቆጣጣሪ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

19) በኬላው በሕገ-ወጥነት የሚያዘውን ቡና ለቁጥጥር መዝግቦ የመያዝ፣ ሳይበላሽ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ያላስረከበ የኬላ ተቆጣጣሪ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## የቡና ጥራትና ግብይት ቁጥጥር አሠራርና አፈጻፀም

### 9.1 የክልል ቡና ጥራትና ግብይት ቁጥጥር

### 9.1.1 የክልል የቡና ጥራት ቁጥጥር

1) በመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት የሚያቀርበው ቀይ እሸት ቡና በተመሳሳይ ደረጃ የቀላና በእለቱ የተሰበሰበ መሆኑን፣ ጀንፈል ቡና ከሆነ በአግባቡ የደረቀና ከባዕድ ነገሮች ነጻ መሆኑ ይረጋገጣል፡፡

2) በአምራች ተሰብስቦ ለግብይት የሚቀርበውን የቡና ቅጠል ተፈጥሯዊ አገልግሎቱን አጠናቆ የተሰበሰበ መሆኑንና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3.3.2 መሠረት መዘጋጀቱን ይረጋግጣል፡፡

3) በአምራቹ እና በአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች የሚከናወነውን የቡና ዝግጅትና አያያዝ ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

4) አቅራቢው መሠረታዊ የሆኑና በአምራቹ አካባቢ ሥራ ላይ እንዲውሉ የተዘጋጁ የቡና ጥራት መመዘኛ መስፈርቶችን ያላሟላ ጀንፈልም ሆነ ቀይ እሸት ቡና አለመግዛቱ ይረጋግጣል፡፡

5) የቡና መፈልፈያና የማበጠሪያ እንዱስትሪዎች ጥራቱን የጠበቀ ቡና ለማዘጋጀት አስፈላጊውን ባለሙያ፣ መሣሪያዎችንና የቡና ማዘጋጃ ክፍሎችን ማሟላታቸው ክትትል ይደረግበታል፡፡

6) በየማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች የሚከማች ለአቅርቦት የሚሆን ቡና አያያዝና የጥራት ሁኔታ እንዲሁም መጠን ክትትል ይደረግበታል፡፡

7) በቡና እሴት የሚጨምር እንዱስትሪ በዚህ መመሪያ እንቀጽ 2.6 መሠረት ስለ መዘጋጀቱ ክትትልና ቁጥጥር ይደረግበታል፡፡

8) አቅራቢው ያዘጋጀውን የአቅርቦት ቡና ወደ ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል ሊወስድ ሲል የእርጥበት ይዘትና ያልታጠበ ቡና ሲሆን ደግሞ በተጨማሪ የጉድለት ቆጠራ በማካሄድ (ቅድመ ጥራት ምርመራ በማድረግ) መሄድ ያለበትን እና የሌለበትን ቡና በውጤቱ መሠረት ይወስናል፣

9) ለመጫን የተዘጋጀው ቡና ንፅህናው በተጠበቀና ለቡና መጫኛ አገልግሎት ልዩ ምልክት ባለው ጆንያ መሆኑ ይረጋገጣል፡፡

10) ቡናውን ለመጫን የመጣውን መኪና ደረጃውን የጠበቀ ቡናን ለማጓጓዝ የተቀመጠውን መስፈርት ያሟላ መሆኑ ተረጋግጦ እንዲጭን ይደረጋል፡፡

11) ቡናው የሚሸፈንበት ሸራ ንፁህ፣ ቀዳዳ የሌለውና ወጥ መሆኑን በማረጋገጥ ቡናው በፕሎምፕ ይታሸጋል፡፡
12) ወደ ቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕካለት ወይም ወደ ኤክስፖርት ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች የተሸኘው ቡና መረጃ ተጠናቅሮ ለሚፈለገው አካል ይተላለፋል፡፡
13) ከታጠበ እና ከተፈጥሯዊ/ካልታጠበ ቡና የሚወጣውን ፍሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በተቀመጠው የአወጋገድ ስርዓት መሠረት እንዲወገድ በቅንጅት ይሠራል፡፡
14) ወደ ማንኛውም የአቅርቦት ቡና መጋዘን፣ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ወይም የአገልግሎት ሰጪ መሥሪያ ቦታ በሥራ ሰዓት ገብቶ የቡና ጥራት ቁጥጥር ሥራ ማካሄድ፡፡
15) ቡና የሚጭኑ ተሽከራካሪዎች ቡና በሚያጓጉዙበት ወቅት የቡናን ጥራት ሊያጓድሉ ከሚችሉ እንደ እንስሳት፣ ከሰል፣ ቅባት፣ጋዝ፣ ቆዳ ፣ቅመማ ቅመም እና ሌሎች ምርቶች ጋር ያልተጫነ መሆኑን ይረጋግጣል፡፡
16) ወደ ቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል ወይም ኢትዮጵያ ምርት ገበያ የተሸኘ ቡና የጫነ ተሽከርካሪ በጉዞ ላይ የመገልበጥ አደጋ ደርሶበት በጥራት ላይ ችግር የሚያመጣ ከሆነ በቦታው ላይ በመገኘት አስፈላጊውን የጥራት ምርመራ ይደርጋል፣ በፕሎምፕ ታሽጎ ይሸኛል፡፡
17) በቡና ማከማቻ መጋዘን ውስጥ ከቡና ውጪ ማንኛውንም ምርቶችና ቁሳቁሶች አለመከማቸቱን ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡
18) የተሸኘዉ ቡና ወደተሸኘበት ቦታ በትክልል መድረሱን ክትትል ይደረጋል፣ ይረጋግጣል፡፡
19) በአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ በመገኘት አሰራሩ በተፈቀደው የቴክኒክ አሰራር መሰረት መሆኑን ይረጋግጣል፡፡
20) በአዋጁ አንቀጽ 19 (1) መሠረት ለሃገር ውስጥ ፍጆታ የማይመጥን ቡና በቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ውስጥ ወይም አግባብ ባለዉ የመቆጣጠሪያ ኬላ በሰው ጤናና በአከባቢ ደህንነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ቡና ሲገኝ አግባብ ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ ቡናው በጥንቃቄ እንዲወገድ ለንግድና ጤና ፅ/ቤት ወይም ለሚመለከተዉ የመንግስት ተቋም በፅሁፍ ይገለፃል፡፡

### 9.1.2 የክልል የቡና ግብይት ቁጥጥር

1) ከአነስተኛ አርሶአደር በስተቀር ማንኛውም አምራች ወይም አቅራቢ ወይም የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ወደ ቡና ማዘጋጀትና ማከማቸት ስራ ዉስጥ ከመግባቱ በፊት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያወጣ እና ያሳደሰ መሆኑን ይረጋግጣል፡፡
2) አምራቹና አቅራቢው፣ ከተፈቀደዉ የምርት ዘመን በላይ ቡናውን እንዳያከማቹ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡
3) የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች በተከለሉ መገበያያ ስፍራዎች የሚደረገዉ የቡና ግዢና ሽያጭ በደረሰኝ መሆኑ እና የተስተካከለ የግብይት ስርዓት መስፈኑ ይረጋግጣል፡፡
4) በተከለሉ መገበያያ ስፍራዎች ተገዝቶ ወደ መፈልፈያና ማበጠሪያ ኢንዱስትሪ ሲጓጓዝ የይለፍ ወረቀት ይዘው መሸኘታቸው ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡



ዶ/ር ደበላ ቡቶ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

5) የቡናውን መረጃ በመሸኛ ሰነድ ላይ በትክክል  በመሙላት ታሽጎ በመሸኛው ላይ አግባብነት ባለዉ የክልል አካል ስልጣን የተሰጠዉ የወረዳ ጽ/ቤት ሕጋዊ ማሕተም ተደርጎ ይሸኛል፡፡

6) ሕጋዊ መሸኛ  ይዞ ከመነሻው ከተፈቀደለት የቡና ዓይነት ወይም መጠን ውጭ ጭኖ ስለመጓጓዙ ጥቆማ ከደረሰ መኪናውን ታጅቦ በአቅራቢያዉ ወደሚገኝ የቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከል በማድረስ የታሸገውን ተበጥሶ ይፈተሻል፣ ሕገወጥ ሆኖ ከተገኘ ጭነቱን የጫነ አሽከርካሪ በሕግ እንዲጠየቅ ሪፖርት ለሚመለከተው ይቀርባል፣ ክትትል ይደረጋል፡፡

7) ህገ ወጥ ቡና ጭኖ በኃይል የመቆጣጠሪያ ኬላ ለማለፍ ሙከራ ሲደረግ በአካባቢው በኬላ ሥራ ከተሠማሩ የፀጥታ ኃይሎች ጋር በመተባበር በማስቆም በአካባቢው ወደ ሚገኘዉ የቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከላት አጅቦ የማድረስና አጥፊው በሕግ እንዲጠየቅ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን በዝርዝር ተዘጋጅቶ ለቅርብ ኃላፊ ሪፖርት ይቀርባል፡፡

8) በኬላዎች የሚደረግ የኬላ ምዝገባ ሙሉ መረጃ በአግባቡ መያዝና አግባብ ላለው የክልል አካል ማስተላለፍ ይኖርበታል፡፡

9) የአቅራቢዎችን፣ የአልሚ ባለሃብቶችንና የህብረት ሥራ ማህበራት/ዩኒየኖች ቡና ክምችት በየማዘጋጃ እና ማካማቻ ኢንዱስትሪዎች ድንገተኛ የክምችት ቆጠራና ምርት ክምችት አያያዝ ቁጥጥር ይድረጋል፡፡

10) በክምችት ቆጠራ ወቅት አምራቾችና አቅራቢዎች ከማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች እና ከተከለሉ መገበያያ ስፍራዎች ከገዙት ወይም ከማሳ ካመረቱት፣ አዘጋጅተው ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ከላኩት ወይም በቀጥታ ወደ ውጪ ከላኩት ከበለጠ ወይም ካነሰ፣

ሀ/ ለቡናውን ባለቤት ይህንኑ በጹሁፍ በማሳወቅና የመቀነሱንና መጨመሩን ምክንያት በጹህፍ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲቀርብ ይጠየቃል፤

ለ/ ያለመጨመር ወይም ያለመቀነስ የቀረበው ማስረጃ አሳማኝ ካልሆነ እርምጃ ይወሰድበታል፤

ሐ/ በስሌት የተገኘው የቡና ክምችት ሚዛን በመብለጥም ሆነ በማነስ ከ2 በመቶ እና ከዚህ የሚያንስ ከሆነ በባለስልጣኑ በሚሰጠው የጹሁፍ ማስጠንቀቂያ ይታለፋል፤

መ/ የተጠየቀው ማስረጃ በጹሁፍ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ካልቀረበ፡- የባለቤቱ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ ተደርጎ ለሚመለከተው አካል የንግድ ፈቃዱ እንዲሰረዝ በጹህፍ ያሳውቃል፤ በመጋዘኑ በተጨማሪነት የተገኘ ቡና የአዋጁ አንቀጽ 19(2) በመተላለፍ ተጠርጥሮ ይያዛል፣ የወንጀል ኃላፊነት ክስ እንዲመሠረት ለፖሊስ ማመልከቻ ይቀርባል፡፡

11) የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና የጅምላ እና የችርቻሮ ንግድ መከታተልና መቆጣጠር፣

12) ወደ ማንኛውም የአቅርቦት ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ በሥራ ሰዓት የመግባትና አግባብነት ያላቸውን ሠነዶች የመመልከትና ኮፒ የመውሰድ፣ ፎቶግራፍ የማንሳት፣

13) የተሸኘ ቡና የጫነ ተሽከርካሪ በጉዞ ላይ እክል ቢያጋጥመው በቦታው ላይ በመገኘት አስፈላጊውን የማጣራት ሥራ ይከናወናል፡፡

14) የአዋጁን ወይም የደንቡን ድንጋጌዎች ወይም እነዚህን ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎች መጣሳቸውን ሲረጋገጥ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም ትዕዛዙን ለማውጣት በሚያስፈልገው ጊዜ



እዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)

ውስጥ ቡናው ሊሠወር ይችላል ብሎ ሲገመት ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሕገ-ወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን ቡና ደረሰኝ ሰጥቶ የመያዝ ወይም የቡናውን ናሙና ወስዶ ቡናው የተካማቸበትን መጋዘን የማሸግ፣

15) በህገወጥ ተጠርጥሮ መጋዘን ወይም ሌላ ቦታ ሲታሸግ፦

ሀ/ ታሽጓል የሚል በጉልህ የሚታይ ጽሁፍ፤

ለ/ የታሸገበት ቀን እና ዓም፣

ሐ/ የታሸገበት ምክንያት እና

መ/ የአሻጊው አካል ስምና ማህተም

ተገልጾ በመጋዘኑ ወይም ቡናው ባለበት ክፍል በር ላይ መለጠፍ አለበት፡፡

16) በህገወጥነት ተጠርጥሮ መጋዘኑን ወይም ሌላ ቦታ ያሸገው አካል በመጋዘኑ ወይም በሌላ ቦታ ውስጥ የተገኘውን ቡና በደንቡ አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ አንድ ላይ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ተከትሎ ቡናውን ከተቀመጠ በኂላ የመጋዘኑን ወይም በሌላ ቦታ ያለውን እሽግ ይነሳል፡፡

17) በተራ ቁጥር 16 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 19 (1) መሠረት የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ሲታሸግ በወንጀል ኃላፊነት የተወሰነው ቅጣት እስከሚጠናቀቅ ድረስ ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪው እንደታሸገ ይቆያል፡፡

18) ለሃገር ውስጥ ፍጆታ የማይመጥን ቡና በቡና ማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘን ወይም አግባብ ባለዉ መቆጣጠሪያ ኬላ ሲገኝ በሰው ጤናና በአከባቢ ደህንነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ እነደሚችል አግባብ ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ ቡናው በጥንቃቄ እንዲወገድ ለንግድና ጤና ፅ/ቤት ወይም ለሚመለከታቸዉ የመንግስት ተቋማት በፅሁፍ ይገለፃል፡፡

## 9.2የፌዴራል የቡና ጥራትና ግበይት ቁጥጥር

### 9.2.1 የፌዴራል የቡና ጥራት ቁጥጥር

1) የወጪ ገበያ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች የሚከናወነውን የቡና ዝግጅትና አያያዝ ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

2) የቡና ጥራት ምርመራ ደረጃ ምደባ ማዕከላት የቡና ማካማቻ መጋዘን የሚደረገውን የቡና ክምችት አያያዝ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

3) እሴት በሚጨምሩ የወጪ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች የሚደረገውን ቡና መቁላት፣ መፍጨት፣ ማከማቸት፣ ማሸግ ተግባራት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

4) የቡና ገለባ ወይም የቡና ቅጠል ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች የሚደረገውን የማቀነባበር፣ የማከማቸት፣ የማሸግ ተግባራት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

5) ወደ ማንኛውም የወጪ ገበያ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ መሥሪያ ቦታ በሥራ ሰዓት የመግባትና የቡና ናሙና በመውሰድ ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

6) ቡና በሚጓጓዝበት ወቅት የቡናን ጥራት ሊያጓድሉ ከሚችሉ እንደ እንስሳት፣ ከሰል፣ ቅባት፣ ጋዝ፣ ቆዳ፣ ቅመማ ቅመም ምርቶች እና ሌሎች ቁሳቁሶች ጋር ያልተጫነ መሆኑን ይረጋግጣል፡፡



እዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

7) በኮንቴነር ለሚጫን ቡና በኮንቴይነሩ ቡና ከመግባቱ በፊት ወለሉና ግድግዳው ከባዕድ ሽታ፣ ከኬሚካል ቅሪት የፀዳና ዝገት የሌለው፤ የአየር ማስገቢያ ወንፊት ያለውና በሩ በትክክል የሚከፈትና የሚዘጋ መሆኑ ይረጋገጣል።

8) ወደ ወደብ የተሸኘ ቡና የጫነ ተሽከርካሪ በጉዞ ላይ የመገልበጥ አደጋ ደርሶበት በጥራት ላይ ችግር የሚያመጣ ከሆነ በቦታው ላይ በመገኘት ከፖሊስ የሚሰጥ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ አስፈላጊው የጥራት ምርመራ ይደርጋል።

9) የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች የተመሠከረለት ደረጃውን የጠበቀ የቡና ማዘጋጃ መሣሪያ፣ ብቁ መጋዘን፣ የእርጥበት መለኪያ መሣሪያና የታተመ የምስክር ወረቀት ያላቸው መሆኑ ይረጋግጣል።

10) የወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ቡናን ሊያከማች የሚችል ንፁህ አየር የሚያስገባ፣ የሙቀትና እርጥበት ይዘቱ የማይዋዥቅ እና ለቡና ማከማቻነት ብቃቱ የተመሠከረለት መሆኑን ይረጋግጣል።

11) በቡና ማከማቻ መጋዘን ውስጥ ከቡና ውጪ ማንኛውንም ምርቶችና ቁሳቁሶች አለመከማቸቱ ክትትል ይደረጋል።

12) ማንኛውም ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ የተከማቸውን ቡና አያያዝ በተፈቀደው የቴክኒክ አሰራር መሠረት መሆኑ ይረጋግጣል፣ የአሰራር ክፍተት ሲኖር የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል።

9.3 በአዋጁ አንቀጽ 19 (1) መሠረት የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ውስጥ ወይም አግባብ ባለዉ የቡና መቆጣጠሪያ ስፍራዎች በሰው ጤናና በአከባቢ ደህንነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ቡና ሲገኝ አግባብ ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ ቡናው በጥንቃቄ እንዲወገድ በአካባቢው ለሚገኝ ለንግድና ጤና ፅ/ቤት ወይም ለሚመለከተዉ የመንግስት ተቋም በፅሁፍ ይገለፃል።

### 9.4 የፌዴራል የቡና ግብይት ቁጥጥር

1) ማንኛውም ቡና ለማከማቸት በተፈቀደለት ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ብቻ የሚዘጋጅና የሚከማች መሆኑ ይረጋግጣል።

2) ቡና ወደ ወጪ የሚልኩ የግብይት ተሳታፊዎች ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በአመራጭ የቡና ግብይት ሥርዓት የገዙትን ወይም ያመረቱትን፣ ወደ ውጭ የላኩትን፣ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሸጡትንና በመጋዘን የቀረውን የቡና ክምችት በየጊዜው ቁጥጥር ይደረጋል።

3) ከምርት ዘመኑ ያለፈ የቡና ክምችት ሲገኝ የክምችት ዘመኑ ያለፈበትን ምክንያት፡-

ሀ/ የአቅርቦት ቡና ከሆነ ከክልሉ አግባብ ካላው አካል ማስረጃ እንዲቀርብ ይደረጋል፤

ለ/ የወጪ ቡና ከሆነ ቡናውን ለላመሸጡ ከአቅም በላይ የሆነ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ አደጋ ወይም ጉዳት በቡናው ባለቤት ወይም ንብርት ላይ መድረሱ በማስረጃ ከተረጋገጠ በደንቡ አንቀጽ 37 (8) ከተጠቀሰው የቅጣት ውጪ የጊዜ ገደቡ እንዲራዘምለት ይደረጋል። ከዚህ ወጪ ከሆነ በተጠቀሰው አንቀጽ የተቀመጠው ተፈጻሚ ይሆናል፤

ሐ/ ያለ በቂ ምክንያት ወይም በደንቡ የተቀመጠው የቅጣት የጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ የምርት ዘመን ያለፈበት ቡና ተይዞ እንዲወረስ ይደረጋል።



ኸዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)

4) የወጪ ገበያ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች በመገኘት የቡና ክምችት ቆጠራና ምርት ክምችት አያያዝ ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

5) በክምችት ቆጠራ ወቅት ቡና ላኪዎች ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በአመራጭ ግብይት አሠራር የገዙት፣ ከራሳቸው ማሳ ያመረቱትን አዘጋጅተው ወደ ወደ ውጪ ከላኩት እና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ከሸጡት ተረፈ ምርት ተሰልቶ በክምችት ሊገኝ የሚገባው ቡና ከበለጠ ወይም ካነሰ፣

ሀ/ ለቡናው ባለቤት ይህንኑ በጹሁፍ በማሳወቅና የመቀነሱንና መጨመሩን ምክንያት በጹህፍ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲቀርብ መጠየቅ አለበት፣

ለ/ ላለመጨመር ወይም ላለመቀነስ የቀረበው ማስረጃ አሳማኝ ካልሆነ እርምጃ ይወሰድበታል፣

ሐ/ በስሌት የተገኘው የቡና ክምችት ሚዛን በመብለጥም ሆነ በማነስ ከ2 በመቶ እና ከዚህ የሚያንስ ከሆነ በባለስልጣኑ በሚሰጠው የጹህፍ ማስጠንቀቂያ ይታለፋል፤

መ/ የተጠየቀው ማስረጃ በጹሁፍ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ካልቀረበ፡- የባለቤቱ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ ተደርጎ ለሚመለከተው አካል የንግድ ፈቃዱ እንዲሰረዝ በጹህፍ ይገለጻል፤ በመጋዘኑ በተጨማሪነት የተገኘ ቡና የአዋጁ አንቀጽ 19(2) በመተላለፍ ተጠርጥሮ ይያዛል፣ የወንጀል ኃላፊነት ክስ እንዲመሠረት ለፖሊስ ማመልከቻ ይቀርባል፡፡

6) ወደ ማንኛውም የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ወይም እሴት የሚጨምሩ ኢንዱስተሪዎች ወይም የአገልግሎት ሰጪ መሥሪያ ቦታ በሥራ ሰዓት የመግባትና የቡና ናሙና የመውሰድ፣ አግባብነት ያላቸውን ሠነዶች መመልከት፣ ፎቶግራፍ የማንሳትና ኮፒ የመውሰድ ተግባራት ይከናወናል፡፡

7) ቡና በሚጓጓዝበት ወቅት በህጋዊ መሸኛ ሰነድ መሠረት የተሸኘ መሆኑ ይረጋግጣል፡፡

8) የተሸኘ ቡና የጫነ ተሽከርካሪ በጉዞ ላይ የመገልበጥ አደጋ፣ ብልሽት ወይም ሌላ እክል ቢደርስበት በቦታው ላይ በመገኘት ከፖሊስ የሚሰጥ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ አስፈላጊውን የማጣራት ስራ ይከናውናል፡፡

9) ቡና የሚያጓጉዝ ተሽከርካሪን የማስቆም የመፈተሽ ተግባራት እና አግባብነት ያላቸው ሠነዶች እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡

10) ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማዕከላት ወደ የወጪ ገበያ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች ወይም የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ከምርት ገበያ ማዕከል ወደ ሸማች ክልሎች ወይም የወጪ ገበያ ቡና ጥራት ምርመራና ሰርተፊኬሽን ማዕከል ወደ ወደብ የሚጓጓዝ ቡና ሲጫን ተጣርቶ ይሸኛል፡፡

11) የአዋጁና የደንቡ ድንጋጌዎች ወይም እነሱን ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎች መጣሳቸው ሲረጋገጥ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም ትዕዛዙን ለማውጣት በማያስፈልግበት ጊዜ ውስጥ ቡናው ሊሠወር ይችላል ብሎ ሲገመት ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ህገወጥ ድርጊት የተፈጠመበትን ቡና ደረሰኝ ተሰጥቶ ይያዛል ወይም የቡናውን ናሙና ተወስዶ ቡናው የተከማቸበትን መጋዘን ይታሸጋል፡፡



ኢዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

12) በህገወጥ ተጠርጥሮ መጋዘን ወይም ሌላ ቦታ ሲታሸግ፡-

ሀ/ ታሽጓል የሚል በጉልህ የሚታይ ጽሁፍ፤

ለ/ የታሸገበት ቀን እና ዓ.ም፣

ሐ/ የታሸገበት ምክንያት እና

መ/ የአሸጊው አካል ስምና ማህተም ተገልጾ በመጋዘኑ ወይም ቡናው ባለበት ቦታ በር ላይ መለጠፍ አለበት፡፡

13) በህገወጥነት ተጠርጥሮ መጋዘኑን ወይም ሌላ ቦታ ያሸገው አካል በመጋዘኑ ወይም በሌላ ቦታ ውስጥ የተገኘውን ቡና በደንቡ አንቀጽ 43 (1) ላይ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ተከትሎ ቡናውን ካስቀመጠ በኋላ የመጋዘኑን ወይም በሌላ ቦታ ያለውን እሽግ ያነሳል፡፡

14) በተራ ቁጥር 13 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጁ አንጽ 19 (1) መሠረት የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ሲታሸግ በወንጀል ኃላፊነት የተወሰነው ቅጣት እስከሚጠናቀቅ ድረስ ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪው እንደታሸገ ይቆያል፡፡

15) ለሃገር ውስጥ ፍጆታ የማይመጥን ቡና ሲገኝ በሰው ጤናና በአከባቢ ደህንነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል አግባብ ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ ቡናው በጥንቃቄ እንዲወገድ በአካባቢው ለሚገኝ ለንግድና ጤና ፅ/ቤት ወይም ለሚመለከተዉ የመንግስት ተቋም በፅሁፍ ይገለፃል፡፡

16) ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በሌሎች የግብይት አማራጮች የተገዛ የአቅርቦት/የተዘጋጀ የወጪ ገበያ ቡና በማንኛውም ምክንያት ለሃገር ውስጥ ፍጆታ ሊሸጥ አይችልም፡፡

17) ማንኛውም ቡና ላኪ የቡና ላኪነቱን ሥራ ያቋረጠ እንደሆነ በድርጅቱ ሥም በክምችት የሚገኘውን ቡና የላኪነት ብቃት ማረጋገጫና ንግድ ፍቃዱን መመለሱን በማረጋገጥ ቡናው ወደውጭ እንዲላክ በምርት ገበያው ወይም በስምምነት ለሌላ ላኪ በባለስልጣኑ ልዩ ፍቃድ ሊሸጥ ይችላል፡፡

18) ማንኛውም ቡና ላኪ የውጭ ገበያ ማጣቱ ፡-

ሀ/ የምርት ዘመኑ ከማለቁ አስቀድሞ ለባለስልጣኑ ገበያ ያጣለትን የቡና አይነትና መጠን በደብዳቤ ሲያሳውቅ ወይም

ለ/ በብሔራዊ ባንክ በኩል የሽያጭ ውል ተመዝግቦ ቡና ገዢው በራሱ ጥፋት ውሉን ማቋረጡ ሲረጋገጥ ቡናው ወደ ውጭ እንዲላክ በምርት ገበያው ወይም በስምምነት የሽያጭ ውል ላለው ለሌላ ላኪ በባለስልጣኑ ልዩ ፍቃድ ሊሸጥ ይችላል፡፡

19) ማንኛውም ቡና ላኪ ከውጭ ገበያ ሽያጭ ተርፎ ሳይላክ የቀረ የወጪ ገበያ ቡና ቡናው ወደ ውጭ እንዲላክ በምርት ገበያው ወይም በስምምነት የሽያጭ ውል ላለው ለሌላ ላኪ በባለስልጣኑ የግዢና ሽያጭ መረጃው ተረጋግጦ በልዩ ፍቃድ ሊሸጥ ይችላል፡፡

20) የወጪ ቡና ሽያጭ ውል ጊዜ ይራዘምልኝ የሚል ጥያቄ ሲቀርብ፡-

ሀ/ የፍትሃብሔር ሕግ አንቀጽ 1793 መሰረት ግዴታ እንዳይፈጸም የሚያስችሉ ባለዕዳው አላፊ የማይሆንበት፣ ያልታሰቡና በሌላ ሰው ላይ የሚመጡ ድንገት ደራሽ ነገሮች፣ ውሉ እንዳይፈጸም በመንግስት የማይደረግ ክልከላ፣ እንደ መሬት መናወጽ፣ መብረቅ፣ ማዕበል፣ ይህን የመሳሰለ ፍጥረታዊ ነገሮች፣ የወጪ የውጪ አገር ጦርነትና የአገር ውስጥ ጦርነት መኖርና እና በባለዕዳው



እዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

መሞት ወይም ባልታሰበ ሁኔታ የሚደርስበት ከባድ አደጋ ወይም ጽኑ ህመም መኖሩ ሲረጋገጥ ውሉ እንደሁኔታው እንዲራዘም ይደረጋል።

ለ/ የፍትሃብሔር ሕግ አንቀጽ 1794 መሠረት አስገዳጅ ያልታሰበ ሁኔታ የለም ተብሎ የሚታሰበው በተዋዋዩ ፋብሪካ፣ ቤት፣ ወይም ስራውን ከሚያከናውንበት ባንደኛው መስሪያ ቤቱ ቅርንጫፍ ውስጥ የተደረገ የሰራተኞች አድማ ወይም የመስሪያ ቤቱ መዘጋት ጉዳት፣ የእቃ መወደድ ወይም መርከስ፣ ግዴታ የሚያከብድ አዲስ ህግ መውጣት ሲኖር ነው።

ሐ/ የወጪ ቡና፣ መወደድ ወይም መርከስ በአለም ገበያ ላይ ተፅኖ መፍጠሩ በባለስልጣኑ ሲረጋገጥ ውሉ እንደ ሁኔታው እንዲሻሻል ይደረጋል።

21) የወጪ ቡና ሽያጭ ውል ያለበቂ ምክንያት አለመፈጸሙ ከተረጋገጠ ወይም በባለስልጣኑ የተራዘመ የውል ጊዜ ካልተፈጸመ፡

ሀ/ ላኪው ተጨማሪ ኮንትራት እንዳይፈጽም ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በጹህፍ ይገለጻል።

ለ/ ላኪው የቡና ግዢ እንዳይፈጽም ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ በጹህፍ ይገለጻል እንዲሁም በሌሎች የግብይት አማራጮች የቡና ግዢ እንዳይፈጽም በባለስልጣኑ ተመዝግቦ ይያዛል።

ሐ/ ከላይ በ16 (ለ) የተጠቀሰው ቢኖርም ላኪው ተጨማሪ ኮንትራት እንዳይፈጽም ከተወሰነበት በፊት ለውጪ ሽያጭ ለፈጸማቸው ኮንትራቶች ብቻ ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በአማራጭ ግብይት ግዢ መፈጸም ይችላል።

22) ከምርት ዘመኑ ያለፈ የቡና ክምችት ሲገኝ የክምችት ዘመኑ ያለፈበትን ምክንያት፡-

ሀ/ የአቅርቦት ቡና ከሆነ ከክልሉ አግባብ ካላው አካል ማስረጃ እንዲቀርብ ይደረጋል፤

ለ/ ማንኛውም የታጠበ የአቅርቦት ቡና በምርት ዘመኑ እስከ ነሐሴ ፴ ቀን ድረስ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በአማራጭ ግብይት ውል መሠረት ለቡና ላኪው ስለመቅረቡ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል።

ሐ/ ማንኛውም ያልታጠበ የአቅርቦት ቡና በምርት ዘመኑ እስከ ጥቅምት ፴ ቀን ድረስ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በአማራጭ ግብይት ውል መሠረት ለቡና ላኪው ስለመቅረቡ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል።

መ/ የወጪ ቡና ከሆነ በአሳማኝ ምክንያት አግባብ ካለዉ አካል መረጃ እንዲያቀርብ ይደረጋል፡-

ሰ/ ማንኛውም ቡና አዘጋጅቶ ለወጪ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ለወጪ ገበያ ያዘጋጀውን የታጠበ ቡና የምርት ዘመኑ ማጠናቀቂያ ጊዜ እስከሆነው ጥቅምት ፴ ቀን ድረስ በወጪ ገበያ ስለመሸጡ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል።

ረ/ ማንኛውም ቡና አዘጋጅቶ ለወጪ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ለወጪ ገበያ ያዘጋጀውን ያልታጠበ ቡና የምርት ዘመኑ ማጠናቀቂያ ጊዜ እስከሆነው ጥር ፴ ቀን ድረስ ስለመሸጡ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል።

23) ከላይ በፊደል ተራ (ለ) እስከ ፊደል ተራ (ረ) በተጠቀሱት የጊዜ ገደብ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ያልቀረበ ያቅርቦት ቡና ወይም ወደ ውጭ ያልተላከ የላኪ ቡና በክምችት መኖሩ ሲረጋገጥ፡-



አዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

ሀ/ ምርት ዘመኑ ባለፈ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሚሸጡ ከሆነ የቡናውን በቅጣቱ ዕለቱ በነበረው ተመሳሳይ የቡና አይነት በምርት ገበያ አማካኝ ዋጋ ተሰልቶ ከጠቅላላ ዋጋው ሁለት በመቶ ወይም

ለ/ ከላይ በፊደል ተራ (ሀ) የተጠቀሰዉ ጊዜ ሲጠናቀቅ ቀጥሎ ባለዉ አንድ ወር ውስጥ የሚሸጡ ከሆነ የቡናውን በቅጣቱ ዕለቱ በነበረው ተመሳሳይ የቡና አይነት በምርት ገበያ አማካኝ ዋጋ ተሰልቶ ከጠቅላላ ዋጋው አምስት በመቶ ቅጣት በባለስልጣኑ በተከፈተ ዝግ አካውንት ገቢ ይደረጋል፡፡

24) በቡና ላኪነት ለመሠማራት የተፈቀደለት የቡና ላኪ ቡና ከመግዛቱ በፊት የዓለም አቀፍ የቡና ድርጅት የ (ICO) እና የመ/ቤቱን መለያ ቁጥር ማግኘቱ ይረጋገጣል፡፡

25) ወደ ውጭ የሚላክ ቡና በተሞላበት ጆንያ ላይ የዓለም አቀፍ የቡና ድርጅት (ICO) መለያ ቁጥር፣ የሠርተፍኬት ቁጥር፣ የቡናው ዓይነት፣ የጥራት ደረጃ፣ የቡናው ምርት ዘመን፣ የሚሄድበት አገርና በኢትዮጵያ የተመረተ መሆኑን የሚገልጽ ጽሁፍ መስፈሩን ይረጋግጣል፡፡

## ክፍል አስር

## ህገወጥ ቡና ስለመጠቆም፣ ስለመያዝ፣ ስለውሰኔ አሰጣጥና ስለሽያጭ አፈጻጸም

### 10.1 ስለመጠቆም

#### 10.1.1 የጥቆማ አቀባበል

1) ማንኛውም ሕገወጥ ቡና ጠቋሚ ጥቆማውን ሲያቀርብ የባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ወይም የሕግ አስከባሪ አካል ሠራተኛ የጥቆማ መቀበያ ቅጽ ሞልቶ በመፈረም ኮፒውን ይሰጣል፡፡

2) በግንባር ሳይቀርብ የጥቆማ መረጃ የሰጠ ሰው በሶስት የሥራ ቀናት ወደ ጠቆመበት ቦታ ቀርቦ የጥቆማ ቅጽ ኮፒ ይወስዳል፡፡

3) በጥቆማው መሰረት ህገወጥ ቡናው ከተያዘ ጥቆማውን የተቀበለው አካል ይህንን የሚገልጽ ማስረጃ ለጠቋሚው ይሰጣል፡፡

4) በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ የሆኑ በጋራ ጥቆማ ካቀረቡ በጋራ በአንድ ጥቆማ ቅጽ ይመዘገባሉ፡፡

5) ቀደም ሲል ጥቆማ መረጃ በቀረበበት ጉዳይ ተደርቦ ወይም በድጋሚ የጥቆማ ቅጽ አይሞላም፡፡

#### 10.1.2 የጥቆማ ምስጢራዊነት

1) በሕገወጥ ቡና ላይ የሚደረግ ማንኛውም ጥቆማ እና የጠቋሚው ማንነት አግባብነት ካለው የባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባላው የክልል አካል ሠራተኛ ወይም ኃላፊ በስተቀር ለማንም ሰው ወይም አካል ሚስጢራዊነቱ ይጠበቃል፡፡

2) ባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባላው የክልል አካል የጠቋሚው ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ማናቸውም የመረጃ ብክነት እንዳይኖር ከፍተኛ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡



ዶ/ር ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባላው የክልል አካል የሚቀርብ ማንኛውም ጥቆማ አስገዳጅ ወይም አሳማኝ ሕጋዊ ምክንያት ከሌለው በስተቀር ተቋማዊ ይሆናል፡፡

4) ማንኛውም የባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ሠራተኛ ወይም ህግ አስከባሪ የተቀበለውን ጥቆማ ከላይ በተራ ቁጥር 3 ላይ ከተደነገገው ውጪ መረጃውን በጽሁፍ፣ በቃል፣ ወይም በማናቸውም ዘዴ ለማንኛውም ሰው አሳልፎ የሰጠ ወይም ሚስጢራዊነቱን ያባከነ እንደሆነ አግባብ ባላ ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

5) ባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባላው የክልል አካል ወይም የህግ አስከባሪ ማንኛውንም ጠቋሚ የሚለይበት እንዲሁም ከጠቋሚ ጋር ለሚኖረው ማንኛውም ግንኙነት የተለየ የሚስጢር መለያ ቁጥር ወይም ስም ለእያንዳንዱ ጠቋሚ ይሰጣል፡፡

### 10.2 ስለመያዝ

1) ማንኛውም በሕገወጥነት ተጠርጥሮ የሚያዝ ቡና በደንቡ አንቀጽ 43 (1፣2 እና 3) የተጠቀሱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተለውን አሰራር መከተል ያስፈልጋል፡፡

ሀ/ ጥቆማ የቀረበበት ሕገወጥ ቡና ጥቆማ ከደረሰበት ጊዜ በ24 ሰዓት ውስጥ ተጣርቶ መያዝ አለበት፡፡

ለ/ በሕገወጥነት ተጠርጥሮ የሚያዝ ቡና በሚከተለው ሁኔታ መረጃ መያዝ አለበት፡-

1) ቡናው የተያዘበተ ቦታና ቀን፣
2) የቡናው ዓይነት እና መጠን በኪሎ፣
3) ቡናው የተገኘበት ባለቤት ስም እና ሙሉ አድራሻ እና የሥራ መስክ፣
4) የቡናው ወካይ ናሙና፣
5) ቡናው ሲያዝ የነበሩ ታዛቢዎች ስምና አድራሻ፣

ሐ/ ሕገወጥ ቡና ያለበት ቦታ ከተለየ በኋላ ወደ ሚፈለግበት ሕጋዊ ቦታ እስኪጓጓዝ ድረስ እስከ 5 ቀናት ድረስ አሸጎ በጥበቃ ሊያቆየው ይችላል፡፡

መ/ በሕገወጥነት ተጠርጥሮ የተያዘ ቡና የቡናው ተቆጣጣሪ ባለበት በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ማህተም ወይም የአከባቢው አስተዳደር ማህተም ባረፈበት ወረቀት መግቢያውና መውጫው ይታሸጋል፡፡

ሠ/ የአካባቢ አስተዳደሩ ሕገወጥ ቡና ወደ ሕጋዊ ቦታ እስኪጓጓዝ ድረስ በቦታው ጠባቂ በመመደብ የመጋዘኑን ደህንነት ይጠብቃል፡፡

### 10.3 ስለመወሰን

#### ሀ/ ህገወጥ ቡና ለመወሰን ስለሚቋቋም ኮሚቴ

1) በህገወጥ የተጠረጠረ ቡና፣ ተሽከርካሪ፣ ተጨማሪ ጭነት ሕገወጥ መሆኑ ሲረጋገጥ በባለስልጣኑ የገበያ ቁጥጥር ሰራተኞችና ሀላፊዎች አማካኝነት እንዲወረሱ ተደርጎ ለበላይ አካል ይቀርባል፡፡

2) በህገወጥነት በተጠረጠረ ቡና፣ ተሽከርካሪ፣ ተጨማሪ ጭነት ላይ ቅሬታ ሲቀርብ አጣርቶ የሚወስን 5 አባላት ያሉበት ኮሚቴ በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የበላይ ኃላፊ በየደረጃው



እ.ዱ.ኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)

ይቋቋማል እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካልን የሚመራ የህገ ወጥ ቡና ቁጥጥር ግብረ ሃይል አደረጃጀት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

3) የኮሚቴ አባላት የሚሆኑት ከቡና ግብይት ተቆጣጣሪ ሠራተኛና የስራ ክፍል ኃላፊ ወጭ ማንኛውም የባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል የስራ ኃላፊዎች ሊሆኑ ይችላል፡፡

ለ/ የኮሚቴው አወሳሰን ሂደት

የዚህ አንቀጽ 10.2.1 መሠረት የተቋቋመ ኮሚቴ፡-

1) ከቅሬታ አቅራቢ በማስረጃ የተደገፈ አቤቱታ ይቀበላል፤
2) የግብይት ተቆጣጣሪው ስለጉዳዩ ማስረጃ በጽሁፍና በአካል የእንዲያቀርብ ያድርጋል፣
3) በህጉ መሠረት የቅሬታውን አግባብነት ያጣራል፤
4) ህገወጥ ቡና በመጫን የተጠረጠረ ተሽከርካሪ የመያዝ ድርጊት በደንቡ አንቀጽ 41 ንዕስ አንቀጽ 3 መሠረት መፈጸሙን ያጣራል፣
5) የተጠረጠረው የተሽከርካሪው ባለቤት የህገወጥ ቡና ወንጀል ተሳትፎ እንዳለውና እንደሌለው ያጣራል፣
6) በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት ተሽከርካሪውን በሌላ ወገን በኪራይ ውል ወይም በሌላ አኳኋን ሲያስተላልፍ ተሽከርካሪው በሕገወጥ ድርጊት እንዳይሰማራ ለመከላከል ወይም ለማስቆም ያደረገው ጥረት ወይም የወሰደው እርምጃ ካለ በማስረጃ እንዲረጋገጥ ያደርጋል፣
7) ኮሚቴው የቀረበውን መረጃና ማስረጃ በመመርመር በተጠረጠረው ቡና፣ ተሽከርካሪ፣ ተጨማሪ ጭነት ይወረስ አይወረስ ውሳኔ ወስኖ ለአቤቱታ አቅራቢ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

10.4 ስለሽያጭ

ሀ/ የህገ ወጥ ቡና ግብይት/ሽያጭ አፈጻጸም

1) ህገ-ወጥ ድርጊት የተፈፀመበት ጀንፈል ወይም ቀይ እሸት ቡና በተያዘበት አከባቢ በሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከል ይሸጣል፡፡
2) ህገ-ወጥ ድርጊት የተፈፀመበት የጀንፈል ወይም የእሸት ቡና ሽያጭን በተመለከተ በክልል የሚመለከተው አካል ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ሊወጣ ይችላል፡፡
3) ህገ-ወጥ መሆኑ የተረጋገጠ የሀገር ውስጥ ፍጆታ ወይም የአቅርቦት ቡና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ ይሸጣል፡፡
4) ህገ-ወጥ ድርጊት የተፈፀመበት ቡና የተያዘበት አካባቢ ወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ቡናውን ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ቀርቦ እንዲሸጥ ተወካይ መድቦ ማስፈፀም አለበት፡፡
5) ቡናው ተመርምሮ በተሰጠው ዓይነትና ደረጃ መሠረት ቡናውን ባቀረበው አካል በሚመረጥ አገናኝ አባል በኩል በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ይሸጣል፡፡
6) የኢትዮጵያ ምርት ገበያም ከሽያጭ ጋር የተያያዙ ወጭዎችን እና የአገናኝ አባል ኮሚሽን በማቀናነስ ቀሪውን ገንዘብ ባለስልጣኑ ወይም ቡናዉን የያዘዉ የመንግስት አካል ባቀረበዉ የሒሳብ ቁጥር ገቢ ያደርጋል፡፡



እዱኛ ደበላ በቀ (ጦ...)

7) በህገወጥነት የተወሰነበት ተሸከርካሪ ወይም ከቡና ውጭ ተጨማሪ ጭነት ወይም ምርት በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በግልጽ ጨረታ ይሸጣል፡፡

ለ/ የአበል አከፋፈል

1) ለጠቋሚ የሚከፈል የኮሚሽን አበል ጠቋሚው በሚያቀርበው የተመዘገበ የጠቋሚ ቅጽ ኮፒ እና ቡናውም በጥቆማው መሠረት ስለመያዙ በተሰጠው ማስረጃ መሰረት ይሆናል፡፡

2) ባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ከያዥ እና ለህገወጥ ቡና በመቆጣጠር በቀጥታ ተሳታፊ ተቋማት ስለተረከበው ሕገወጥ ቡና፣ ተሸከርካሪ፣ ተጨማሪ ጭነት ወይም ምርት ማስረጃ ማስጠት አለበት፡፡

3) ለያዥ እና ለህገወጥ ቡና በመቆጣጠር በቀጥታ ለሚሳተፉ ተቋማት የኮሚሽን አበል ክፍያ የሚፈጸመው ቡናውን ይዘው ገቢ ያደረጉበት ማስረጃ ሲቀርብ ይሆናል፡፡

4) ለጠቋሚ፣ ለያዥ እና ህገወጥ ቡና በመቆጣጠር በቀጥታ ለሚሳተፉ ተቋማት የኮሚሽን አበል ክፍያ የሚከፈለው በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የበላይ ኃላፊ ፊርማ ይሆናል፡፡

5) ጠቋሚ ወይም ያዥ የኮሚሽን አበል ክፍያ ሳይፈጸምለት ቢሞት ወይም ቢጠፋ መብቱ ህግ ለሚፈቅድላቸው ወራሾች/ባለመብቶች ይተላለፋል፡፡

6) የኮሚሽን አበል ክፍያ የይርጋ ጊዜ ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ስድስት ወር ድረስ ነው፡፡

## ክፍል አስራ አንድ

## የቡና ናሙና አፈቃቀድና አላለክ ሥርዓት

### 11.1 ለቅድመ ሽያጭ የሚላክ የቡና ናሙና አፈቃቀድ

1) የቡና ላኪዎች ለሚሸጡት ቡና ለዉጭ ሀገር ገዢ ደንበኞቸው ከሽያጭ ውል በፊት እና በኋላ ይሁንታ ለማግኘት ለአንድ ገዢ በየቡና ዓይነቱ እና ደረጃ እስከ አንድ ኪሎግራም ድረስ የቡና ናሙና ፈቃድ ሳያስፈልግ በራሱ ወይም ማንኛውንም የመልዕክት መላኪያ ተቋማትን ተጠቅሞ መላክ ይችላል፡፡

2) ማንኛውም ላኪ የቡና ናሙና ለቅድመ ሽያጭ ለመላክ የወቅቱን የታደሰ የንግድ ፈቃድ መያዝ አለበት፡፡

3) ማንኛውም ላኪ የሽያጭ ዉል ከፈጸመ በኃላ የቅድመ ጭነት ናሙና ለመላክ የተዋዋለበትን ሰነድ ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

4) ለአንድ የቡና ዓይነትና ጥራት ደረጃ ለሚፈጸም ሽያጭ ኮንትራት የሚደረግ የናሙና ምልልስ ድግግሞሽ ከሦስት ጊዜ በላይ ሊሆን አይገባም፡፡

5) ላኪዎች በፖስታ ቤት የቡና ናሙና ለመላክ ሲቀርቡ ፖስታ ቤቶቹ የላኪውን የዘመኑን የታደሰ የቡና ላኪነት ንግድ ፈቃድ የቡና ናሙናው በዓይነትና በጥራት ደረጃው መሠረት እስከ አንድ ኪሎ ግራም ድረስ በናሙና መላኪያ ፕላስቲክ ታሽጎ ስለቡናው ምንነት የሚገልጽ፣ የገዢ ኩባንያ ስም እና አድራሻ በትክክል የያዘ መሆኑን አረጋግጠዉ ማስተናገድ ይኖርባቸዋል፡፡



እዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤችዲ)

### 11.2 ቡናን ለማስተዋወቅ ስለሚደረግ የቡና ናሙና አፈቃቀድ

1) የቡና ላኪዎችና ቡናን ለማስተዋወቅ የሚፈልጉ መንግሥታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቡናን በማስተዋወቅ በታወቁ ኢግዚቢሽንና ኮንፍረንስ ላይ ሲሳተፉ ቡናን በጥሬ፣ በተቆላ ወይም በተፈጨ መልክ ይዘዉ መዉጣት ወይም በአመቺ ማጓጓዣ ማጓጓዝ ይችላሉ፣
2) ማንኛው በቡና ኤግዚቢሽን ኮንፈረንስ ተሳታፊ ለባለስልጣኑ የተሳትፎ ዝርዝር መረጃ በማቅረብ በአጠቃላይ ከሁሉም የቡና ዓይነትና ደረጃ እስከ 10 ኪሎ ግራም ድረስ ቡና ይዞ መውጣት ይችላል፣
3) በተራ ቁጥር 2 እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣና በዓለም አቀፍ የቡና ንግድ ትርኢትና ባዛር ለመሳተፍ የትእይንት ቦታ ለተከራዩ ላኪዎች በአጠቃላይ ከሁሉም የቡና ዓይነትና ደረጃ የኩነቱ ስፋት እና ፋይዳ ታሳቢ ተደርጎ በቡና ላኪ እስከ 100 ኪሎ ግራም ቡና ይዞ መውጣት ሊፈቀድ ይችላል፣
4) ቡና በአለም አቀፍ መድረኮች የሚያስተዋውቁ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በአጠቃላይ ከሁሉም የቡና ዓይነትና ደረጃ እስከ 10 ኪሎ ግራም ቡና በባለስልጣኑ ፍቃድ ይዞ መውጣት ይችላሉ፣
5) ማንኛው በቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፈረንስ ተሳታፊ ለባለስልጣኑ ጥያቄ አቅርቦ ለማስፈቀድ የቡና ላኪነት ፍቃድ ያለው መሆን አለበት፣
6) ማንኛውም ላኪ የቢዝነስ ትስስሩን ለማጠናከር የቢዝነስ ጉብኝት ለማካሄድ ወደ ገዢ ሀገራት ለሚያካሄደው ጉዞ በአጠቃላይ እስከ 10 ኪሎ ግራም ድረስ ለባለሥልጣኑ ጥያቄ አቅርቦ በማስፈቀድ ይዞ መዉጣት ይችላል፣

## ክፍል አስራ ሁለት

## ለቡና መያዣ ስለሚውል ጆንያ

### 12.1. ስለጆንያ አመራረት፣ አጠቃቀምና አወጋገድ

1) ለማንኛውም ቡና ለመያዣነትና ማጓጓዣ የሚውል ጆንያ ከቃጫ የተሰራ፣ ያልተቀደደ፣ ንጹህ እና ከማንኛውም የኬሚካል ቅሪት የጸዳ መሆን አለበት፣
2) ማንኛውም የቡና መያዣ ጆንያ ተመርቶ ለገበያ ሲቀርብ የተመረተበት ዘመን እንዲሁም መለያ የንግድ ምልክት በሚፈለገው ቀለም በግልጽ በሚታይ መልኩ በጆንያው ላይ መታተም ይኖርበታል፣
3) ማንኛውም ለቡና መያዣነት የሚውል ጆንያ ከውጭ ሀገር ሲገባ ደረጃውን የጠበቀና ከፀረ-ተባይ ኬሚካል ቅሪት የፀዳ ስለመሆኑ ዕውቅና ካለው ላብራቶሪ የተረጋገጠ ማስረጃ ለባለስልጣኑ ከውጪ አስገቢው ማቅረብ አለበት፣
4) ማንኛውም ለቡና መያዣነት የሚውል ጆንያ በአገር ውስጥ ሲመረት ደረጃውን የጠበቀና ከፀረ-ተባይ ኬሚካል ቅሪት የፀዳ ስለመሆኑ ህጋዊ ዕውቅና ባለው ላቦራቶሪ በየተረጋገጠ ለባለስልጣኑ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፣



አዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

5) ለቡና ለመያዝና ለማጓጓዝ ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም ጆንያ አገልግሎት መስጠት ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ የጥራት ሁኔታው እየተረጋገጠ ቢበዛ ከሁለት ዓመት በላይ ማገልገል የለበትም፣
6) በአቅርቦት ቡና ግብይት ሂደት ለመያዣነት የዋለው ጆንያ በሁለት አመት ውስጥ አራት ዙር አገልግሎት ላይ ሊውል እንደሚችል ታሳቢ በማድረግ የዚህን አማካኝ ዋጋ ተሰልቶ ቡና ገዢው ከቡና መግዣ ዋጋው ላይ ይህን አማካኝ የጆንያ ዋጋ ተጨማሪ በማድረግ ለአቅራቢ ይከፍላል፡፡
7) የቡና ግብይቱ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ሲፈጸም አማካኝ የጆንያ ዋጋ በምርት ገበያው አማካኝነት ከገዢው ሂሳብ ተቀንሶ ለአቅራቢው ይከፈላል፡፡
8) የቡና መያዣ ጆንያ አመታዊ አማካኝ ዋጋ ባለስልጣኑ የሚመራው የምርት ገበያ፣ የላኪና የአቅራቢ ማህበራትን በሚያሣትፍ ኮሚቴ ይወሰናል፡፡
9) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የአገልግሎት ጊዜውን በጨረሰ የቡና መያዣ ጆንያ ለቡና መያዣነት እንዳይውል ባለስልጣኑ ቁጥጥር በማድረግ እርምጃ ይወስዳል፡፡
10) የአገልግሎት ጊዜውን ባይጨርስም በጥንቃቄ ጉድለት የቡናን ጥራት በሚያጓድሉ ኬሚካሎች ወይም በሌሎች ባዕድ ነገሮች የተበላሸ መሆኑ ከተረጋገጠ ባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ጆንያው ለቡና መያዣነት እንዳይውል ያደርጋል፡፡
11) የቡና መያዣ ጆንያ የጥራት ስታንዳርድ በተመለከተ ባለስልጣኑ ዝርዝር ተጨማሪ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል አስራ ሦስት
## የንፁህ ቡና መጠን

### 13.1. የቡና ዝግጅት በየደረጃውና ዓይነት ተቀናሽ የመጠን ለውጥ አወሳሰን

በየደረጃው ንፁህ ቡና ለማግኘት የማጠብ፣ መቀሸርንና የወጪ ቡና ዝግጅት የሚቀንሰውን መጠን የአለም አቀፍ ቡና ድርጅት የተቀበለውን መጠን ተግባራዊ ይሆናል፡፡

1) 100 ኪሎ ግራም እሸት ቡና ወደ ታጠበ ቡና ከነገለፈቱ ሲዘጋጅ 20 ኪሎ ግራም ይወጣል፡፡
2) 100 ኪሎ ግራም የታጠበ ቡና ከነገለፈቱ ወደ የተቀሸረ ንጹህ የታጠበ ቡና ፍሬ ሲዘጋጅ 80 ኪሎ ግራም ይወጣል፡፡
3) 100 ኪሎ ግራም ጀንፈል ቡና ወደ የተቀሸረ ንጹህ ያልታጠበ ቡና ፍሬ ሲዘጋጅ 50 ኪሎ ግራም ይወጣል፡፡
4) 100 ኪሎ ግራም ያልታጠበ የአቅርቦት ቡና ወደ ወጪ ቡና ሲዘጋጅ 85 ኪሎ ግራም ይወጣል፡፡
5) 100 ኪሎ ግራም ዲካፌኔትድ ጥሬ ቡና 105 ኪሎ ግራም ጥሬ ቡና ይወጣል፡፡
6) 100 ኪሎ ግራም በመደኛ የተቆላ ቡና 119 ኪሎ ግራም ጥሬ ቡና ይሆናል ፡፡
7) 100 ኪሎ ግራም ዲካፌኔትድ የተቆላ ቡና 125 ኪሎ ግራም ጥሬ ቡና ይሆና፡፡
8) 100 ኪሎ ግራም ሶሉብል ቡና 260 ኪሎ ግራም ጥሬ ቡና ይሆናል
9) 100 ኪሎ ግራም ዲካፌኔት ሶሉብል ቡና 273 ኪሎ ግራም ጥሬ ቡና ይሆናል፡፡



ጀዱኛ ደበላ ቡቴ (ፒኤች ዲ
ዋና ዳይሬክተር

## ክፍል አስራ አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 14.1.የተከለከሉ አሠራሮች/ድርጊቶች

ማንኛውም በቡና ግብይት እና አገልግሎት ሰጪነት ላይ የተሰማራ፡-

1) ያልበሰለ ወይም አረንጓዴ ቡና እንዲለቀም ወይም ለግብይት እንዲውል ማድረግ፣
2) መርቡሽ ቡና ማዘጋጀት፣መግዛት፣መሸጥ፣ ማከማቸት ወይም ማጓጓዝ፣
3) ያለ ብቃት ማረጋገጫና የፀና ንግድ ፈቃድ በቡና ግብይት እና አገልግሎት መስጠት ላይ መሳተፍ፤
4) በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለዉ የክልል አካል ከፈቀደዉ የቴክኒክ አሰራር ዉጭ በማናቸዉም ዘዴ ቡናን ማዘጋጀትና ማከማቸት፣
5) የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡናን ከኤክስፖርት ቡና ጋር ማደባለቅ፣
6) ትክክለኛ የእርጥበት ደረጃ ያልያዘና ጥራቱን ያልጠበቀ ቡና ወደ ማዕከላዊ ገበያ መሸኘት፣
7) ንፅህናውን ባልጠበቀ ተሽከርካሪ ላይ ቡና መጫን፣ማጓጓዝና የመሸኛ ወረቀት መስጠት፣
8) የተለያየ ባህሪና ዝግጅት ያላቸውን የአቅርቦት ቡናዎች በማደባለቅ ለጥራት ምርመራ ደረጃ ምደባ ማዕከላት ማቅረብ፤
9) በቡና ጥራት ምርመራና ደረጃ ምደባ ማዕከላት ውስጥ ለቡና ጥራት የሚሰጠውን ደረጃ ማዛባት፣
10) የተገባውን የሽያጭ ዉል ያለበቂ ምክንያት መሰረዝ፣
11) ለወጭ ገበያ የቡና ሽያጭ ዋጋ አሳንሶ የመሸጥ/ የሽያጭ ዉል ማስመዝገብ፣
12) የቡና አልሚ ባለሀብት በራሱ ካለማውና ከአርሶ አደሩ በልማትና ግብይት ትስስር ከገዛው ቡና ውጪ ቡና መግዛት፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝና መሸጥ፣
13) ቡና አልሚ ባለሀብት ወይም አምራች አርሶ አደር በይዞታው ካዘጋጀው ወይም በልዩ ሁኔታ አስፈቅዶ በባለስልጣኑ ወይም በክልል አግባብ ባለው አካል እውቅና ከተሰጠው ማከማቻ ውጪ ቡና ማከማቸት፤
14) ከመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከል ወይም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ከተፈቀዱ የአማራጭ ግብይት ውጪ ቡና መሸጥ ወይም መግዛት፣
15) ቡናን ከአንድ የምርት ዘመን በላይ ማከማቸት፣
16) በባለስልጣኑ ካልተፈቀደ በስተቀር ለውጪ ገበያ የሚመጥን ቡናን በጥሬውም ሆነ ቆልቶ ወይም ቆልቶ በመፍጨት በሀገር ውስጥ ገበያ መሸጥ ወይም ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚውል ቡና ቆልቶ ወይም ቆልቶና ፈጭቶ ለውጭ ገበያ የማዋል፣
17) ሆን ብሎ አለአግባብ ጥቅም ለማግኘት በቡና ጥራትም ይሁን ግብይት አሳሳች ድርጊት መፈፀም፣
18) በማንኛውም ማጓጓዣ ቡናን ያለፍቃድ ማጓጓዝ፣የተከለከሉ ድርጊቶች ናቸው፡

### 14.2.የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች

1) የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት መመሪያ ቁጥር 01/2010 በዚህ መመሪያ ቁጥር 002/2011 ተሽሯል።



ዶ/ር ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

2) የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

**14.3. መመሪያ ስለማሻሻል**

ባለስልጣኑ ይህንን መመሪያ ማሻሻል ይችላል።

**14.4. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ መስከረም 22 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዱኛ ደበላ (ፒኤች.ዲ)

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለስልጣን

መስከረም 22 ቀን 2012 ዓም



እዱኛ ደበላ ቦቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር